# "ኑ ... ሥራውን እዩ"

## የወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ታሪክ ወንጌላዊው ለተመስገን ሳህለ እንደተረኩለት

ነሐሴ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

© Copy Right 2016 - Ethiopian Kale Heywet Church Communication and Literature Department

All Rights Reserved. No portion of this book may be reproduced in any form what so ever, except for a brief cuotations in reviews, with out the written permission of the publisher.
አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር በምንም አይነት ሁኔታ ቢሆን ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት፣ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረጽና ማራባት በፍጹም የተከለከለ ነው:: ለምርምር ሥራና ለጥናታዊ ጽሑፎች ማጎልበቻነት ውሱን ሃሳቦችን ከመጽሐፉ ውስጥ መውሰድ የተፈቀደ ነው::

*"ኑ ሥራውን እዩ"*

*"Come and see His works!"*

Narrated By – Evangelist Kedamo Mechato

Author – Temesgen Sahle

ትረካ - በወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ

ጽሕፈት እና ዝግጅት - ተመስገን ሳህለ

አርትኦት - ሽመልስ ኃይሌ

እርማት እና ትየባ - ሳባ በየነ

ትየባ እና የገጽ ቅንብር - ነጻነት ጴጥሮስ

የሽፋን ገጽ ቅንብር እና የውስጥ ገጽ ዲዛይን - ወንድወሰን ፊሊሞን

የስቱዲዮ ፎቶ - ናሆም ፎቶ

አሳታሚ:- የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ኮምኒኬሽን እና ሥነ ጽሑፍ መምሪያ

Publisher: Ethiopian Kale Heywet Church Communication and Literature Department
ስልክ 0115 505908
ፖ.ሳ.ቁ 5829 አዲስ አበባ
Email: temesgensahle@yahoo.com

መታሰቢያ:-

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ታሪክ ውስጥ እንደ ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ያሉ ታላላቅ የወንጌል አርበኞች
እየተነሱ ለብዙዎች መዳን ምክንያት እንዲሆኑ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆነው እነርሱን
ላፈሩት ከነናቸውም ሆነው ለደገፉት ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች
(ለአቶ ሳህሌ ጆፌ፣ ለአቶ በቀለ ወርቁ፣ ለባለቤቶቻቸው ወ/ሮ ብዙነሽና ወ/ሮ ታደለች ...)
በሙሉ መታሰቢያ ይሁን::

የአሳታሚው ማስታወሻ:-

ይህ መጽሐፍ በሳማሪታንስ ፐርስ ተቋም መልካም ልግስና እና ድጋፍ የታተመ መጽሐፍ ነው:: መጽሐፉ ከታተመበት ዓላማ አንዱ በዚህ ታሪክ ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ሥራ በተተኪው የቤተክርስቲያን ትውልድ ህይወት እንዲቀጥል ለማድረግ ነው:: በዚህ መሠረት ከታሪኩ ባሻገር ከመጽሐፉ የሚገኘው ገቢ በከፊል ወንጌላዊ ኬዳሞ ለጀመሩት የወንጌል አገልግሎትን እና አገልጋዮችን በገንዘብ የመደገፍ ሥራ ይውላል::

Publishers Note:-

This Book is published by the generous support of Samritians Purse Organization. One of the purposes for the publication of the book is to attempt that the work of the Lord started in the life of Evangelist Kedamo to continue in the life of the church's next genereation. Therefore in addition to the story told, partial amount of the money generated from sales will be allocated for the purpose of Evanglists Supporting Ministry started by Evangelist Kedamo.

## ምስጋና

ይህ መጽሐፍ ወንጌላዊ ኬዳሞ እንደ ገለጹት ገና ከናታቸው ማህጸን ጀምሮ የመረጣቸው ለራሱ ሥራም የለያቸው በአስደናቂ ውጣ ውረዶች ውስጥ አብሮ ሆኖ እያሳለፈ የብዙ የወንጌል ገድላት ባለቤት ያደረጋቸው እግዚአብሔር የሠራው ሥራ የተተረከበት ነው:: ደግሞም ታሪኩ እንዲጻፍ ከታሰበበት ጊዜ አንስቶ አሁን ታትሞ እርሶ እጅ እስከገባበት ድረስም እግዚአብሔር ታላቅ ድጋፍ በሥራው ለተሳተፉት ሁሉ አድርጓል:: ስለሆነም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ቀዳሚ ምስጋናችንን ለእርሱ እንሰጣለን::

ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ በብዙ ትዕግስት ብዙ ዋጋ በመክፈል ታሪኩን የተረኩትን ወንጌላዊ ኬዳሞን በተለይም በሁለት አይኖቻቸው እንደሚገባ ለማንበብ በሚቸግራቸው እድሜ ላይ የመጽሐፉን ገጾች በአጠቃላይ አንድ በአንድ በጥንቃቄ እያነበቡ መስተካከል ያለበትንም እየጠቆሙ ብዙ ትጋት ማሳየታቸው ምንም እንኳን የታሪኩ ባለቤት ቢሆኑም እርሳቸውንም ስለወንጌሉ ላሳዩት ቅናት ይህ መጽሐፍም የግል ዝናቸው እንዲተረከበት ሳይሆን የእግዚአብሔር ሥራን እንዲዘከር ስላሳዩት ትጋት በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ስም ልናመሰግናቸው እንወዳለን::

ይህ መጽሐፍ በብዙዎች ለመነበብ የሚበቃ መጽሐፍ እንደሚሆን ታምኖበት የተዘጋጀ ቢሆንም ያማረ የገጽ ቅንብር ከባለ ቀለም ፎቶዎች ጋር ተካተውበት በዳጎስ የገጽ ብዛት እንዲቀርብ ያስቻለው ግን የወንጌላዊ ኬዳሞ ቀደምት የአገልግሎት አጋር የሆነው እና በታላቁ ወንጌላዊ ቢሊ ግራሃም የተመሰረተው ሳማሪታንስ ፐርስ (The Samaritans Purse) ያደረገው የኅትመት ድጋፍ ነው:: የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያንም ለዚህ ቀደምት የአገልግሎት አጋሯ የሆነ ተቋም የላቀ ምስጋናዋን ታቀርባለች:: ብሎም ተቋሙን በኃላፊነት በሚመሩበት ወቅት ለወንጌላዊ ኬዳሞ አገልግሎት መሳካት የሚረዱ ድጋፎች እንዲደረጉ ከዚህም ባለፈ ተቋሙ ለዓመታት የቤተ ክርስቲያናችን አጋር ሆኖ እንዲቀጥል ያደረጉትን የተቋሙ የቀድሞ መሪ ፍራንክሊን ግራሃም እና አጋራቸው ኬን አይዛክስን ለማመስገን እንወዳለን:: ከዚሁ ጋር በተያያዘም ሳማሪታንስ ፐርስ የቀረበውን የኅትመት ድጋፍ ጥያቄ ተቀብሎ አወንታዊ ምላሽ እንዲሰጥ ጥያቄውን በቤተ ክርስቲያናችን ስም የተቋሙ ዋና ቢሮ ድረስ በመውሰድ ላቀረቡት የቀድሞው የቤተክርስቲያኒቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ እና የልማት ኃላፊ ለነበሩት አቶ ደስታ ደምሴ ምስጋናችንን እናስተላልፋለን::

ይህ መጽሐፍ ሊጻፍ እንደሆነ ሲሰሙ በደስታ አስተያየታቸውን ለላኩት አቶ ፖል እና ወ/ሮ ላይላ ቢልስኪ፣ ለአቶ ሜርል ዳይ እና ወ/ሮ ጁን ዳይ፣ ለወንጌላዊ አቡዬ ቲርካሶ እና ለአቶ ደምሴ ማጼ እንዲሁም መጽሐፉ ከተጻፈ በኋላ አስተያየታቸውን ለሰጡት አቶ ሽፈራው ወልደሚካኤል፣ ዶ/ር ደስታ ሔሊሶ እና የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ዋና ጸሐፊ አቶ ኩርሴ ሽፈዋ ስላደረጉት ቀና ትብብር እናመሰግናቸዋለን:: በተለይም ዶ/ር ደሴታ ሄሊሶ ከአገር ለመውጣት ዝግጅት እያደረገ በነበረበት ወቅት የደረሰውን የመጽሐፍ ቅጂ ከዳር እስከዳር በጥልቀት በማንበብ ከመጽሐፉ የአጻጻፍ ስልት አንስቶ እስከ የታሪካዊ እና የቋንቋ አጠቃቀም ድረስ የነበሩትን ግድፈቶች በማረም ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ሃሳቦች በመጠቆም ታላቅ እገዛ አድርጓል:: ስለሆነም ዶ/ር ደስታን ስላደረገው የላቀ እገዛ ከልብ ልናመሰግነው እንወዳለን::

ይህ መጽሐፍ መጻፍ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለዓመታት የትየባ ሥራውን ላከናወነችው እልፍ ስትልም በገጽ ቅንብር እና እርማት ሥራው ለተሳተፈችው ወ/ሮ ነጻነት ጴጥሮስ፣ በመጽሐፉ ዝግጅት ወቅት በቴፕ የተቀዱ የወንጌላዊ ኬዳሞ ትረካዎችን ለቀናት አቀርቅራ በመጻፍ ወደ ወረቀት

የገለበጠችው ብሎም ሙሉ የአርማት ሥራውን ከአንድ ጊዜ በላይ በማድረግ ጥራቱን እንዲጠብቅ የተጋችው እና በርካታ የመጽሐፉ ክፍሎችንም በመተየብ አስተዋጽኦ ላበረከተችው ወ/ሮ ሳባ በየነ፤ በስተመጨረሻም በመጽሐፉ ዝግጅት መጨረሻ ላይ መጥቶ የመጽሐፉ አርታኢ በመሆን መጽሐፉ በአፋጣኝ እንዲታተም ልዩ ልዩ የዝግጅት ተሳትፎዎች በማድረግ አስተዋጽኦ ያበረከተው ሽመልስ ኃይሌ እና ሌሎችም በኮምኒኬሽንና ሥነ ጽሑፍ መምሪያ የሚያገለግሉ አጠቃላይ ሠራተኞች ስላከናወኑት ስኬታማ ተግባር ላቅ ያለ ምስጋና ይቀርብላቸዋል፡፡ በስተመጨረሻ የመጽሐፉን የሽፋን ገጽ እና የውስጥ ገጽ የማጠቃለያ የቅንብር ሥራ የሠራውን የጌጃ ቃለ ሕይወት አገልጋይ የሆነው ወንድም ወንደሰን ፊሊሞንን እግዚአብሔር ይባርከህ ለማለት እንሻለን፡፡ መጽሐፉ ለኅትመት ዝግጁ ከሆነ በኋላም በተዋጣለት ጥራት እንዲታተም ያደረገውን የሁልጊዜ የቤተክርስቲያናችን የኅትመት ሥራ አጋር ርኆቦት ማተሚያ ቤት የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ኮምኒኬሽንና ሥነ ጽሑፍ መምሪያ

# የአዘጋጁ ምስጋና

ይኸን መጽሐፍ እንድጽፍ ለመረጠኝ በጸጋው ሞልቶም አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ህያው አምላክ እግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ:: ድግሞም እኔ የመጀመሪያውን የታሪኩን በረከት እንድካፈል በአጋጣሚ ሳይሆን በዓላማ ዕድሉን እንዳገኝ ስላደረገኝ ዘለዓለማዊ ስሙን እባርካለሁ::

ከዚያም ታሪካቸው በኔ እንዲጻፍ ለፈቀዱት ባለ ታሪኩ ወንጌላዊ ኬዳሞ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ:: በመጽሐፉ መጻፍ ሂደትም አንድም ቀን ሳይከፉብኝ ከሚገባኝ በላይ በታላቅ አከብሮት ስለያዙኝ እያመሰገንኩ በወንጌላዊው ቤት ሁል ጊዜ በተገኘሁ ቁጥርም ተሽቆጥቁጣ ታስተናግደኝ የነበረችውን ባለቤታቸውን ወ/ሮ ከበቡሽ መኮሮን (ሰላምን) እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክሽ ልላት እወዳለሁ::

ይህንን መጽሐፍ መጻፍ ስጀምር ጀምሮ አብራኝ ለሆነችው የትዳር አጋሬ በኋላም መጽሐፉን በተዋጣለት ሁኔታ ጽፌ ማጠናቀቅ እንድችል አብራኝ ለተጨነቀችው ብሎም ብርቱ ጸሎት ላደረገችው እመቤቴ ስሂን ጌታቸው እና የሁል ጊዜ ደጋፊዎቼ በተለይም በመንፈሳዊ ህይወት እንዳድግ ላገዘችኝ እናቴ ወ/ሮ አበራሽ ታከለ እና የሥነ ጽሑፍ ሰው እንድሆን አርአያ ለሆነኝ ላበረታታኝ ከዚያም የመጀመሪያ አድናቂዬ ለሆነው አባቴ አቶ ሳህለ ጥላሁን ብሎም ውድ ቤተሰቦቼ በአጠቃላይ ስላደረጉልኝ ድጋፍ ሞቅ ያለ ምስጋናዬ ይድረሳቸው:: በምን መልኩ መመስገን እንዳለባቸው ባላውቅም ሌሎች ሲያደርጉት ስላየሁ ስማቸውን እዚህ ጋ ለመጥቀስ ለደፈርኩት ልጆቼ ረደኤቴ ተመስገን እና ዜማ ተመስገንም ምስጋና አቀርባለሁ::

ይህን መጽሐፍ የመጻፍ ሥራ በእጄ እንዳለ ሲያዩ ላበረታቱኝ የቀድሞም ሆነ የአሁን አለቆቼ ብሎም ሌሎች ሥነ ጽሑፍ ወዳድ ወገኖች፤ ከመጽሐፉ ጋር በተያያዘ እና ስለባለታሪኩ ሊገለጹ ይገባቸዋል የሚሏቸውን ሃሳቦች በማቀበል እገዛ ላደረጉልኝ በርካታ ወገኖችንም በአጠቃላይ ስም በመዘርዘር ጊዜ ሳላጠፋ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ:: በተለይም ከረጅም ጊዜያት ጀምሮ መንፈሳዊ ምክርም ሆነ ሌላ ድጋፍ በማድረግ ሁልጊዜ የበለጠ እንድሠራ ለሚያበረታቱኝ የረጅም ዘመናት አለቃዬ አቶ ኩርሴ ሸፈኖ እና የአሁኑ የቅርብ አለቃዬ ዶ/ር ወይታ ወዛን ስለእገዛቸው ላመሰግናቸው እሻለሁ:: ከመጽሐፉ ዝግጅት ሥራ ጋር በተያያዘም የታለያየ ድጋፍ እና ምክር ለሰጡኝ በተለይም ጸጥታ ባለበት ቦታ ሆኜ ለመጻፍ ስፈልግ ያለክፍያ በማዕከሉ እንዳርፍ ለፈቀዱልኝ የኩሪፍቱ ማዕከል ሥራ አስኪያጅ አቶ ኤርሚያስ ግርማ እና ያስተናገዱኝ የማዕከሉ ሠራተኞች የኩሪፍቱ ማዕከል በሚያዝበት ጊዜም በአዲስ አበባ ባለ የእንግዳ ማረፊያ ቤቷ መሽጌ አስፈላጊው መስተንግዶ እየተደረገልኝ እንዳርፍ ላደረገችው እህት ጺጋ ወንድሙ እና ቤተሰቦቿ ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ::

ይህን መጽሐፍ አዘጋጅቼ እንድጨርስ ለጎተጎቱኝ፣ በልዩ ልዩ መስኮች ደጋፍ በማድረግ ላገዙኝ የምሠራበት መምሪያ ባልደረቦቼ በሙሉ እና ታላቅ ፍቅር በማሳየት እገዛ ለሚያደርጉልኝ አብሬያቸው በመሥራቴ ደስ ለምሰኝባቸው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች በአጠቃላይ ሞቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ:: በልዩ ልዩ የህይወት አጋጣሚ እየተገናኘን በዛመናት መካከል ቁጥራቸው በዝቶ እዳ ለሆኑብኝ በብዙ መልኩ ድጋፍ ለሚያደርጉልኝ ሴት እና ወንድ ወዳጆቼ በአጠቃላይ፤ ሁል ጊዜ በጸሎታቸው ለሚደግፉኝ ወንድሞቼ እና እህቶቼ (ስም ለመዘርዘር ስለከበደኝ ትቼው) በተለይም ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ያህል ለእኔ መጸለይን የአገልግሎት አደራዋ አድርጋ ለምትደግፈኝ እህቴ ስሜነሽ ሙሉጌታ ምስጋና ለማቅረብ እሻለሁ::

ከዚህም በተቀረም ጅምላ ጨራሹ ምስጋናዬ ያልደረሰው ሰው እንደማይኖር በማሰብ ካለም የማይገባው ብቻ መሆኑን እርግጠኛ በመሆን የምስጋና ዝከሬን አበቃለሁ:: መልካም ንባብ!

ተመስገን ሳህለ

# ማውጫ


ታላቅ እድል በአጋጣሚ (የአዘጋጁ ማስታወሻ) .......................... 15
መቅድም .................................................................. 19
የኔ ታሪክ አይደለም ................................................... 21

ክፍል ፩

ምዕራፍ ፩
በሻሾን የተተከለው ችግኝ ............................................. 27
ምዕራፍ ፪
ከድቅድቅ ጨለማ ..................................................... 37
ምዕራፍ ፫
ብርሃኑ ሲበራ ......................................................... 43
ምዕራፍ ፬
ጋሼ ሳህሌ ጆፌ ........................................................ 50
ምዕራፍ ፭
የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት እና የአገልግሎት ጅማሬ .................... 54
ምዕራፍ ፮
የወንጌል ጥሪ እና ዘመቻ ጌዴኦ ........................................ 67
ምዕራፍ ፯
ጋብቻ ................................................................... 83
ምዕራፍ ፰
በወንጌል ጥሪ መጽናት እና ዘመቻ ጌዴኦ ምዕራፍ ሁለት ................ 89
ምዕራፍ ፱
የባለቤቴ ህመም እና የኩየራ ቆይታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪነት ወደ
አስታማሚነት .......................................................... 98
ምዕራፍ ፲
ሁለተኛው ጋብቻ ...................................................... 107
ምዕራፍ ፲፩
እንደገና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት (በዱራሜ ጠዛ) .................. 110
ምዕራፍ ፲፪
ድንገተኛ የወንጌል ዘመቻ ወደ አቶ አሹሮ መኖደር እሸጎላ .............. 114
ምዕራፍ ፲፫
ማረቆ 1954-1955 ................................................. 120
ምዕራፍ ፲፬
እንደገና ወደ ራስ መመለስ ............................................ 128
ምዕራፍ ፲፭
ወደ ቀደመው ጥሪ መመለስ ............................................ 134

ምዕራፍ ፲፮
ወደ ቦቢ.ቾ መሻገር ........................................................ 137
ምዕራፍ ፲፯
ከቦቢቾ ወደ አዲስ አበባ ማሰብ ................................................ 147


## ክፍል ፪

ምዕራፍ ፲፰
የኢትዮጵያ መንግስት ሁኔታና የለውጥ አዝማሚያ ........................ 161
ምዕራፍ ፲፱
በአዲስ አበባ መደላደል ........................................................ 171
ምዕራፍ ፳
ጌጃ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም GBI ................................................ 177
ምዕራፍ ፳፩
የጠላት ማስፈራራት እና የእግዚአብሔር ጥበቃ ለቤተ ክርስቲያን ...... 184
ምዕራፍ ፳፪
ጎጆ እና በቅሎ በአዲስ አበባም ተገኘ .......................................... 192
ምዕራፍ ፳፫
ነዶ በነዶ .... ............................................................................ 200
ምዕራፍ ፳፬
ከሰማርያ ወደ ዓለም ዳርቻ የመዘርጋት ጅማሬ (ኬንያ) ................. 207
ምዕራፍ ፳፭
መብዛት .................................................................................. 211
ምዕራፍ ፳፮
በኢየሱስ ዱካዎች ላይ መራመድ ................................................ 217
ምዕራፍ ፳፯
"ቃለ ሕይወት ሞተች" አለኝ ጌታ .............................................. 224
ምዕራፍ ፳፰
እኔ ወደ ቦናሻ ጌታ ግን ወደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ እና ካናዳ ............ 229
ምዕራፍ ፳፱
ኮምኒዝም ወደቀ ...................................................................... 239
ምዕራፍ ፴
የአውሮፓ የአገልግሎት ቆይታ .................................................... 245
ምዕራፍ ፴፩
ኅብረት እና መቀባበል ለታላቅ ስኬት ........................................ 250
ምዕራፍ ፴፪
ከጌጃ ... ወደ ኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ........................................ 258


## ክፍል ፫

ምዕራፍ ፴፫
ሥራ አለ፤ በጀት የለም .......................................................... 275

ምዕራፍ ፵፬
ኢትዮጵያን በቁመቷም በወርዷም መድረስ ............................ 282
ምዕራፍ ፵፭
እንደገና ወደ ስካንዲኔቪያን /ሰሜን አውሮፓ/ ............................ 287
ምዕራፍ ፵፮
የታላቁ አገልግሎት ታላቅ ፈተና ............................ 292
ምዕራፍ ፵፯
የብሔራዊ ወንጌላዊነትና ዋናው ጽሕፈት ቤት ............................ 300
ምዕራፍ ፵፰
የቃለ ሕይወት ዋና ጽሕፈት ቤት ቢሮን ለመልቀቅ መወሰን ............ 305
ምዕራፍ ፵፱
የብዙዎች አባት / እንደገና ወደ አሜሪካ ............................ 310
ምዕራፍ ፶
ከሃምሳ ዓመታት በኋላ ከሙሉ ጊዜ አገልግሎት መሰናበት ............ 318
ምዕራፍ ፶፩
ነጻ አገልግሎት ............................ 322
ምዕራፍ ፶፪
የታደለች ሞትና የኔ እንደ ንስር መታደስ ............................ 328
ምዕራፍ ፶፫
ሠላም ተገኘች ............................ 336
ምዕራፍ ፶፬
በልጅ መፈተን ............................ 341
ምዕራፍ ፶፭
የመጨረሻው ምዕራፍ ............................ 345

## ክፍል ፬

የወንጌላዊ ኬዳሞ የአገልግሎት ስጦታዎች ............................ 357
1. ወንጌል መስበክ ............................ 358
2. ማስተማር ............................ 361
3. ምክር ............................ 366
4. እርቅ ............................ 372
5. ጸሎት ............................ 379

የታሪኩ ማስቀጠያ ምዕራፍ ............................ 385

የአገልግሎት አጋሮች ስለ ወንጌላዊ ኬዳሞ ምን ይላሉ ............................ 393

# ታላቅ እድል በአጋጣሚ (የአዘጋጁ ማስታወሻ)

የወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶን ታሪክ በጽሑፍ ማስፈር ታላቅ ዕድል ነው፡፡ በተለይም እንደ እኔ ለ6 ዓመታት የወንጌላዊውን ሕይወት እያሰለላሰሉ እና በሚያደርጉት ሁሉ ውስጥ እንደ አንድ የታማኝ የእግዚአብሔር ባሪያ መስፈርት ወንጌላዊውን እያሰቡ መኖር፤ በስብከትም፣ በትምህርትም፣ በምክርም ጣልቃ ስማቸውን እያነሱ ለሌሎች መናገር እንዳች ቁርኝትን ብሎም የሕይወት ምሳሌና የሕይወት ጉዞ ፈለግ መከተልን ስለሚያሳይ መታደሌን ከመጻፉም ያለፈ ያደርገዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የመጀመሪያው በኔ የተጻፈ ሙሉ መጽሐፌ የወንጌላዊ ኬዳሞ ግለ ታሪክ መሆኑ ሌሎች ጸሐፍት የሚቀኑበት ጸሐፊ እንዳደረገኝም ይሰማኛል፡፡ ከኔ በብዙ መልኩ የተሻሉ እና የላቀ ልምድ ያላቸው ብዙዎችም የወንጌላዊውን ታሪክ ለመጻፍ ፈልገው ጥያቄ እንዳቀረቡ እና እንዳልተሳካላቸው ሳይ እኔ ታሪካቸውን እንድጽፍ እድል ማግኘቴ እግዚአብሔርን አጥብቄ እንዳመሰግን የሚያደርገኝ መሆኑን ያስገነዝበኛል፡፡

በእርግጥ የወንጌላዊ ኬዳሞን ታሪክ ለመጻፍ የተመረጥኩት በሰዎች አይደለም፤ ቅዱሳን መጻሕፍት የጻፉትን አባቶች በመረጠው ቅዱስ መንፈስ እንጂ፡፡ ይህን የምለው ለማጋነን ሳይሆን የሆነውን ወይም ሁኔታውን ሳይ የሚገባኝ እንደዛ ስለሆነ ነው፡፡

እኔ ከወንጌላዊ ኬዳሞ ታሪክ እና ማንነት ጋር መተዋወቅ የጀመርኩት ገና ታዳጊ እያለሁ የወንጌላዊው መንፈሳዊ ቀራጥነት እና የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የላቀ አገልግሎት አድናቂ በሆነችው የክርስትናም ሆነ የስጋ እናቴ ወ/ሮ አበራሽ ታከለ (አቫዬ) አማካይነት ነው፡፡ ብርቱ ክርስቲያን የሆነችው እናቴ ወንጌላዊ ኬዳሞን ከልብ ታደንቃለች፡፡ በስብከታቸው ጣልቃ የተናገሩትን ለቀም አድርጋ ይዛ መጥታ በኩራት ስለወንጌላዊው ቆፍጣና አገልጋይነት ታጫውተን ነበር፡፡ "ኬዳሞ ውጪ አገር ሊያገለግሉ ሄደው በውጪ ያሉትን ማስቲካ እያኘኩ፣ እግራቸውን አነባብረው የሚቀመጡ ለእግዚአብሔርም ለቃሉም ክብር የማይሰጡትን ክርስቲያኖች ሳይፈሩ 'በጌታ ቤት ማስቲካ እያኘካችሁ እግራችሁን አጣምራችሁ ነው ወይ የምታመልኩት? በሉ ትፉ!' ብለው ተቆጡልኛ፡፡ ... በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ እኮ ማንም ቅጥ ያጣ አለባበስ ለብሶ መግባት አይችልም፤ በመጣበት እግሩ ይመለሳታል እንጂ!" እያለች ቃልዋን በእንቅስቃሴ አስደግፋ የሰማችውን የወንጌላዊውን ተግባር እና ስብከት ታካፍለን ነበር፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላም በወጣትነቴ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት መጽሐፍ እንድጽፍ ሳይሆን ሌሎች የጻፉትን እንድሸጥ ተቀጠርኩ፡፡ በዚሁ ሥራዬ ሳቢያም በታላላቅ የቤተ ክርስቲያኒቱ ጉባዔያት ላይ ለመገኘት በቃሁ፡፡ ከዚያም በቤቱ ተወልጄ እንዳድግ አድርጎኝ ለከበረ ዓላማው የሚፈልገኝን ጌታ ለማገልገል ዳተኛ የሆንኩትን ሰው ለመግራት በየማለዳው ከሥራ በፊት ከታላላቆቹ የእግዚአብሔር ሰዎች ከመጋቢ ዮሐንስ ባሳና፣ ከአቶ ኩርሴ ሽፈኖ፣ ከወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ እና ከሌሎችም የእግዚአብሔርን ቃል የመማርና ሕይወታቸውን በቅርብ እያዩ ከብርታታቸውም ሆነ ከድካማቸው እውቀት የመቅሰም ዕድል እንደ እንጀራ ከፊቴ ዘረጋልኝ፡፡ ታላቅ ዕድል ገጠመኝ!

በቦቢቾ በተካሄደ አንድ ታላቅ ጉባዔ ላይም ወንጌላዊ ኬዳሞ ተገኝተው የጉባዔተኛውን ልብ የነካ መልዕክት ሲያቀርቡ እና ቅራኔ ውስጥ የነበሩ ቤተ ክርስቲያናትን በሥልጣን ገስጸው በማስታረቅ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ልብ ሲያሳርፉ ማየትና ማድነቅ ቻልኩ፡፡ ወንጌላዊ ኬዳሞ በቁጡነታቸው እና ላመኑበት ሟች በመሆናቸው በብዙዎች የሚፈሩ ቆፍጣና ሰው እንደሆኑ ብሰማና ባይም ለኔ ግን ሁል ጊዜ የቤተሰቦቼን ደህንነት የሚጠይቁኝ፣ የአክብሮት ሰላምታም የማይነፍጉኝ፣ ሁል

ጊዜ ቆፍጣና እንደሆኑ አንድም ቀን ደከመው ዝግ ብለው ሲሄዱ አይቻቸው የማላውቅ፤ ፊታቸው የማይለወጥ፣ የተሳሳተ ነገር ነው ብለው ያመኑበትን ነገር በጉባዔም ሆነ በግል ጭውውት ወቅት ሳይናገሩ የማያልፉ፤ ከሚግባቧቸው ሰዎች ጋር ሲሆኑ ምንም ለረጅም ጊዜያት ባያቆዩትም ተደራርበው በሚታዩት እና ከጎን ባለ የወርቅ ጥርሶቻቸው ብልጭታ ደስታን ከሚረጭ ፈገግታ ጋር መቀለድ የሚወዱ፤ ለሰዎች የማበረታቻ ቃላትን ለመወርወር ቸል የማይሉ ሰው እንደሆኑ አየሁ:: መጽሐፋቸውን ጽፌ የመግቢያ ጽሑፌ ላይ እንደማሰፍረው ሳላውቅም እርሳቸውን እና ሌሎች እራሳቸውን እንደትንሽ በሚያዩ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች መካከል እራሴን በማግኘቴም እግዚአብሔርን ስለሰጠኝ እድል ከልቤ አመስግኛለሁ:: ይባስ ብሎም ወንጌላዊ ኬዳሞ በተገኙበት ያቀረብኩት "አትፍሩ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ የማለዳ መልዕክት እንደተጠናቀቀም ወንጌላዊው ተነስተው መልዕክቱ በኮምኒስቱ መንግስት ዘመን እንዴት የጠቀማቸው እንደነበር በማስታወስ የማጽኛ መልዕክት አስተላለፉ:: እኔም በወንጌላዊ ኬዳሞ የመመስገንን ዕድል በማግኘቴ በጣም ተደሰትኩ፤ ለእርሳቸው ያለኝ አክብሮትም ከቀድሞው ጨመረ::

ከዕለታት በአንዱ ቀን አንድ ማለዳ ላይም የወቅቱ አለቃዬ 50ኛ የአገልግሎት ክብረ በዓላቸው የሚከበርላቸውን ወንጌላዊ ኬዳሞን ታሪክ በአጭሩ እንዲያዘጋጅ መታዘዙንና እርሱ ከመናፍቃዊ ትምህርቶች እና አስተማሪዎች ጋር በሚያደርገው ግብግብ ብዕሩ ባተሌ እንደሆነችበት ገልጾ እኔ ባዘጋጅ የተሻለ እንደሆነ አሳወቀኝ:: እኔም በታላቅ ደስታ ከኮተቤ መምህራን ኮሌጅ በቀሰምኳት እውቀት ተጠቅሜ ቃለ መጠይቅ አድርጌአቸው የወንጌላዊውን ታሪክ በአጭሩ አዘጋጀሁ:: ታሪኩ ተቀባይነት አግኝቶም በክብረ በዓሉ ላይ ተቀባይነት ባላቸው አንድ የጌጃ አባት አንባቢነት ለታዳሚው ቀረበ:: የኔ ትርፍም ኬዳሞ በቃለ መጠይቁ ወቅት ገነት ሆቴል ወስደው የጋበዙኝ የበግ ጥብስ ብቻ ሆነች::

ከዓመታት በኋላም ብዙዎች ታሪካቸውን እንዲጽፉ ሲጎተጉቷቸው የነበሩት ወንጌላዊ እግዚአብሔርም ታሪኩን ቢጽፉት እንደሚወድ አምነው፤ ታሪካቸው የእግዚአብሔር እና የቤተ ክርስቲያን ስለሆነ በቤተ ክርስቲያናቸው አማካኝነት ተጽፎ እንዲሰራጭ ጥያቄ አቀረቡ:: የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎችም ደፍረው የሚያዝዙት ታሪክ ጸሐፊ ስላጡ ታሪክ ጸሐፊነቱ (በወቅቱ የመጀመሪያ ዲግሪዬን በስነ ጽሑፍ ዘርፍ አጠናቅቄ ስለነበር) ወደ እኔ እንዲመጣ ግድ ሆነ:: እኔም የኬዳሞን ታሪክ መጻፍ ምን ማለት እንደሆነ ባውቅም ከራሳቸው ከወንጌላዊው አንደበት የተሰማ ነው በሚባለው "ቶሎ ለመድረስ ቀስ ብሎ መሄድ" ብሂል መሠረት በዝግታ ታሪኩን ልጽፈው ጀመርኩ:: በዚሁ ጊዜም በእጄ ስላለው ሥራ እና የወንጌላዊ ኬዳሞ ታሪክ እንዴት በውጣ ውረዶች እና የጌታ ድንቃ ድንቅ ጣልቃ ገብነቶች ያሸበረቀ እንደሆነ ለቅርብ አለቃዬ አጫውቼው ነበር:: ሆኖም በመዘግየቱ የተሰላቹት ወንጌላዊ ታሪኩን የሚጽፍ ሌላ ሰው እንዲፈለግ ሃሳብ አቀረቡ:: ሆኖም ይህን የሰማው አለቃዬ ያንን ታሪክ ለመጻፍ ምን ያህል ደስተኛ እንደሆንኩ እና የወንጌላዊ ቢሊ ግራሃምን ታሪክ ከመጻፍ የወንጌላዊ ኬዳሞን ታሪክ መጻፍ እንደምመርጥ መናገሬን አስታውሶ እኔ ብጽፈው መልካም መሆኑን ነገሮ አሳመናቸው:: እኔም መጻፌን ቀጠልኩ:: አሁንም በዝግታ!

ይህንን ታሪክ እየጻፍኩም ሁለት ጊዜያት ከድኅረ ምረቃ ተቋማት ተመረቅሁ፤ አንድ ጊዜ አገባሁ፤ ሁለት ልጆችም ወለድሁ:: በእርግጥ ለወንጌላዊ ኬዳሞም ሦስተኛ ትዳራቸውን የሚይዙበት፣ በአስደናቂ የጌታ ጥበቃ ውስጥ እያለፉ ለብዙ ሺዎች ሕይወት መነካት እና መለወጥ ምክንያት የሚሆኑበትን ዕድልም ሰጠኋቸው:: እርሳቸውም ለዓመታት በታላቅ ትእግስት በኔ ላይም ፍጹም በመተማመን አንድ ቀን በቁጣ እንድፈጥን ሳይናገሩኝ (ቀጠሮ ይዘን በመቅረታችን እኔና የመጽሐፉ አርታኢ ከደረሰን አባታዊ ቁንጥጫ በስተቀር)፤ ሁል ጊዜ ተገናኝተን እስክንለያይ ጸልየውልኝ ተቀብለው ጸልየውልኝ እየሸኙኝ፤

በቤታቸው እልፍ ሲልም ወደ ካፍቴሪያ እየወሰዱ እየጋበዙኝ አብረን ተጓዝን:: አንድ ጊዜ የታክሲ አስር ብር መቀበሌንም አልረሳም::

በዚሁ ታሪክ የመጻፍ ሥራ ሂደትም እኔና ወንጌላዊ ኪዳሞ አብረን ሻሾን ድረስ አምርተናል:: እኔ የእርሳቸውን መኪና እየነዳሁ እርሳቸው ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወታቸው የሠራውን እየተረኩልኝ፤ እልፍ ሲልም መንገድ ላይ እንድንወስዳቸው ለምነውን ላሳፈርናቸው ሰዎች ወንጌል እየመሰከሩ ተጉዘናል:: በሻሾን ከወንጌላዊው ጋር አብረን አገልግለን (እርሳቸውን ሻሾን ማድረሴ ከአገልግሎት ከተቆጠረ)፤ አብረን በአንድ አልጋ ተኝተናል፤ መብራት በሌለበት ምድር እራሳቸውን በቃሉ የማስታጠቅ ልማዳቸው እንዳይታጎል በሌሊት ተነስተው እንደ ማዕድን ቆፋሪ ባትሪ ግንባራቸው ላይ ሰክተው ቃሉን ሲያነቡም አብሬ ተቀምጬ አጥንቻለሁ፤ በማለዳ ወፎች ሲንጫጩም አጠገባቸው ጋደም ካልኩበት በክርን ደቁሰው "ተነስ ተነስ ወፎች ለምስጋና ቀደሙን!" ብለውኝ አብረን ጸልየናል:: በሆሳእና ካገለገሉ በኋላ የተሰጣቸውን ማርም ተካፍለን ወደየ ቤታችን ወስደናል:: ብቻ ለብዙ ጊዜያት አብረን በማሳለፍ ይህ ሥራችን ሙሉ እንዲሆን በብዙ ጥረናል:: እግዚአብሔርም ሲረዳን አይተናል::

በሄድንበት ሁሉ ለኪዳሞ ታስቦ የተበረከተውን በረከት እየተቋደስኩ ወደ እርሳቸው ከሚመጡ ሰዎችም ሆነ ከኪዳሞ ከራሳቸው ታላቅ አክብሮት እየተለገሰኝ ተጉዣለሁ:: ወንጌላዊ ኪዳሞ እኔ ከእርሳቸው ጋር አብሬ መቆየቴን በደስታ እንደታላቅ እድል ቆጥረው መቀበላቸው ለኔ ታላቅ በረከት ሆኖልኛል:: በእርግጥ እኔም በእርሳቸው ፊት ሞገስ ለማግኘት ወደ አባት እናቴ አምላክ ጸሎት አድርሼ መሄዴን አልደብቃችሁም:: እናም ታላቅ ሞገስ በእርሳቸው ፊት አግኝቼ የጠየቅኩትን ሁሉ ሊመልሱ ወይም ሊያሟሉ ጥረዋል:: መኪናቸውን ስነዳ ድልድይ በሌለበት ወንዝ ተሻግሬ ሻሾን ስገባ፣ አራት ጊዜ ጎማ ሲፈነዳና ስቀይር አድናቂዬ ሆነው እያሞገሱ፤ ከዚያም የጻፍኩትን ሳሳያቸው በደስታ እያነበቡ ስለተሠራው ሁሉ ጌታን እያመሰገኑ መጽሐፉ ተጻፈ::

በእነዚሁ ዓመታትም ያለዕድሜዬ ወደ ኋላ በርካታ አስርት ዓመታትን ሄጄ ኪዳሞ በሻሾንው የአባታቸው ደጃፍ እንደ ትልቅ ሰው እየሆኑ ሲጫወቱ፤ ከፋሺስት ኢጣሊያ ቦምብ ሸሽት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሲሰደዱ፤ አረኝነት ሜዳ ላይ ዝናብ ሲደበድባቸው፤ ጎርምሰው ዘመድ ወዳጅ ሲያስቸግሩ እና ለመሸፈት ሲያቅዱ፣ በትጋት ሠርተው በእናታቸው ሲመረቁ፣ በሰይጣን ተመርረው የሕይወት አቅጣጫቸውን ሲቀይሩ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው የሻሾንው ወይፈን ሲሰኙ፣ አደብ ገዝተው ትጉህ ተማሪ ሲሆኑ ሁሉ በምናቤ አየሁ::

የመጀመሪያውን ስብከታቸውንም በቦቢቾ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች መካከል ተቀምጬ በማድመጥ አብሬ አነባሁ:: በመስቀሉ ፍቅር ተነድፈው ብራቸውንና የሚወዷት ጊደራቸውን ሰጥተው ስላልረኩ እራሳቸውን ለወንጌል አገልግሎት ሲለዩ እና ጌታ ወደ ወደደው እንዲልካቸው ዋሻ ውስጥ ተንበርክከው ሲግጹትም አደመጥሁ:: ኪዳሞ ለወንጌል ዘመቻ ጌዴኦና ማረቆ ሲዘምቱ፤ ባለቤታቸውን ሲያስታምሙም ኩየራ ሄደው በዛም የወንጌል ብርሃናቸውን ሲለኩሱ ተከትያቸው ሄጃለሁ:: አብሬ ወደ [illegible]ቢቾ ሄጄ ከዚያም ወደ ጊጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተከትዬ መጣሁ:: የወንጌላዊው የአገልግሎት ቀስት ሸቅብ መስፈንጠሯን ቀጥላ ወደ የቅርብ ጎረቤቷ ኬኒያ ብሎም ወደ ሩቅ እና ቅርብ ምዕራቦቹ አሜሪካ፣ ካናዳ እና እንግሊዝ ስታመራም እኔም አብሬ ያለቪዛ በረርኩ::

ሕይወት አልጋ በአልጋ አልነበረችምና ኪዳሞ የሚወዷቸውን ባለቤቶቻቸውን ሲለዩ አብሬ አዘኜ ልጃቸው ዳዊት ሲጠፋ አፋልጌ ሣራ ስትለያቸውም ከቤተሰቡ ጋር አንብቼአለሁ:: በአገሪቱ ታሪክ አስከፊው የሽብር እና የጦርነት ዘመን ግድያ ደጃፋቸውን ሲያንኳኳ፤ በተገደሉ ወጣቶች አስከሬን

መካከል በሞት ጥላ ውስጥ ሲያልፉም በእሳት ውስጥ መንገድ አለው እያልኩ አብሬአቸው ወደ መልካሙ ዘመን ተጓዝኩ፡፡ ፈተና በዝቶ ዝለት ሲገዳደራቸው፣ ቤተ ክርስቲያን ደከማ ጭንቀት ሲከብድባቸውም ከጎናቸው ነበርኩ፡፡

ኬዳሞ በትጋት እንዲያገለግሉት ለብዙ ፍሬም እንዲበቁ እግዚአብሔር ያዘጋጃቸውን ነጭና ጥቁር፤ ሴትና ወንድ የወንጌል አርበኛ ጀግኖችንም በየምዕራፉ እየተዋወቅሁ እግዚአብሔርን ለመከሩ ስለሰጣቸው ሠራተኞች አመሰገንኩት፡፡ ወንጌላዊው በጽናት አንድ ክፍለ ዘመን ያህል እንዲያገለግሉ በብዙ አቅጣጫ እንዲበረቱ ያስቻሏቸውን ልዩ ልዩ በረከቶች ቆጥሬም ታማኙን አምላክ ባረክሁ፡፡

ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ሳይቀር በብዙ መልኩ ብዙዎችን ከጎናችን አስነስቶ ይኸው እንዲህ ያማረ የታሪክ መዘክር እንዲኖረን ያደረገው አምላክ ስሙ ብሩክ ይሁን፡፡ እኔም እያንዳንዷን የኬዳሞ ታሪክ አንጓ በተሻገርኩ ቁጥር ለዚህ እማኝ እንድሆን የመረጠኝን አምላኬን (አንዳንዴ ጽሑፌን አቁሜ ተንበርክኬ) አመሰግኛለሁ፡፡ እናንተም እንድትባረኩበት እመኛለሁ፡፡

ይህ መጽሐፍ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን እያበበ ከመጣው በራስ የተጻፈ ግለ ታሪክ (Autobiography) የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ (genre) የሚመደብ መጽሐፍ ነው፡፡ ስለሆነም በታሪኩ ውስጥ የቀረቡ ሃሳቦች ሁሉ በባለታሪኩ ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ የተተረኩ እና ከተጻፉ በኋላም በወንጌላዊው ይሁንታ የተሰጠባቸው ናቸው፡፡ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ምሁራን "አንድ የጥበብ ሰው በመጀመሪያ የራሱን ስሜት ያልነካውን ጥበባዊ ሥራ የአንባቢያኑን ስሜት እንዲነካ ጠብቆ ማቅረብ የለበትም፡፡" እንዲሉ፤ በመጽሐፉ ውስጥ ያሰፈርኳቸው ሃሳቦች በሙሉ ግን ለኔ ስሜት ትርጉም የሰጡኝ እና በብዙ መልኩ የሕይወት አቅጣጫዬን መስመር ለማስያዝ የምገቱኝ እጅግ የተማርኩባቸው አስደናቂ የእግዚአብሔር ሥራ መዘከሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም በዚህ መጽሐፍ እኔ ከማንም አስቀድሜ ተባርኬአለሁ፤ ከሁላችሁም ቀድሜም ስቄአለሁ፤ አልቅሻለሁም፡፡ እናንተም እንደምትማሩበት፣ እንደምትባረኩበት፣ እንደምትደሰቱበት እና የእግዚአብሔርን ሥራ እንደምታዩበት ተስፋዬ ጽኑ ነው፡፡

እግዚአብሔር ይባርካችሁ!

ተመስገን ሳህለ



# መቅድም

ይህ መጽሐፍ ምንም እንኳን የአንድ የወንጌል አገልጋይ የህይወት ታሪክ ቢሆንም በውስጡ ግን በርካታ ተያያዥ ታሪኮች በከፊል ወይም በሙሉ ተተርከውበታል:: ወንጌላዊው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ከስድስት አስርት ዓመታት በላይ ያገለገሉ በዕድሜ አኩያዊ ስለሆኑ ታሪካቸው በሙሉ የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ታሪክ አካል ነው:: ኤስ. አይ. ኤም. ኢትዮጵያም የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጅማሬ መንስኤ እና ለአመታት የቤተ ክርስቲያኒቱ ወንድም ሆኖ ለዓመታት የዘለቀ ተቋም እንደመሆኑ በተለይም ወንጌላዊው በአንድ ወቅት በዚሁ የሚሲዮን ተቋም አገልጋይ ሆነው ማሳለፋቸው ተቋሙን የወንጌላዊው ታሪክ አካል ሲያደርገው፤ የተጻፈው ታሪክም በአንድ ወቅት በአንድ ስፍራ የተፈጸመ የተቋሙ ታሪክ እንዲሆን አስችሏል:: ከዚህም ባሻገር የወንጌል አማኟ ቤተ ክርስቲያን እያበበች የነበረበት ዘመን ላይ የተፈጸመ እንደመሆኑ የወንጌላዊው ታሪክ ከበርካታ ወንጌላዊያን አማኝ ቤተክርስቲያናት ጋር የተያያዘ እና አልፍ ሲልም ወደ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እና ልዩ ልዩ ባህላዊ እምነቶች ብሎም የእስላሞች መስጊድ ሳይቀር ዘልቆ የገባ በመሆኑ የአገራችን ክርስትና እድገት ታሪክ አካልም ነው::

ከዚህም ባሻገር ወንጌላዊ ኪዳሞ በንስር አይናቸው የኖሩባቸው መንግስታትን ገጽታዎች የሚመረምሩ ስለነበሩ በትረካዎቹ ውስጥም በወንጌላዊው መነጽርነት የሦስት የአገራችን መንግስታት የአገዛዝ ገጽታ በመጠኑ ቀርቦበታል:: ይሄም ታሪኩን ከቤተክርስቲያን አጥር አስወጥቶ አገራዊ ያደርገዋል::

ወንጌላዊ ኪዳሞ በአገልግሎት ስኬት ማማ ላይ ሲወጡ የማማውን መሰላል ለብቻቸው ጡብ ጡብ ብለው ያጠናቀቁት ሳይሆን በእያንዳንዷ ምዕራፍ ላይ ከጅማሬው አንስቶ እግዚአብሔር በርካታ የራሱን ሰዎች ከትዳር አጋሮቻቸው አንስቶ እስከ የውጪ የወንጌል መልዕክተኛ ሚሲዮናውያን እና የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት አጋሮች ድረስ አዘጋጅቶ በብዙ አቅጣጫ እንዲደግፏቸው አድርጓል:: እነዚህ ሰዎችም ሁሉም የዚህ የእግዚአብሔር ሥራ የተተረከበት መጽሐፍ አካል እና ባለታሪክ ናቸው:: በዚህ መጽሐፍም ከመጽሐፉ ዋና ዓላማ ባልራቀ መልኩ የአንዳንድ ከወንጌላዊ ኪዳሞ ጋር የህይወት ቁርኝት የነበራቸው ግለሰቦች ታሪክ በመጠኑ እና የነሱም ታሪክ እንዲሁ ቢጻፍ የሚል ምኞት ለመፍጠር ያህል ጥቂት ገጽ እየተቆነጠረለት ተተርኳል::

ይህ ታሪክ መጻፍ በተጀመረበት ወቅት ወንጌላዊ ኪዳሞ ሰምንት አስርት ዓመታትን የደፈኑ የዕድሜ ባለጸጋ እንደመሆናቸው አንቱታን ተጎናጽፈዋል:: ሆኖም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከታሪካቸው ጅማሬ አንስቶ በጉልምስና እድሜያቸው ወደ አዲስ አበባ እስከ ተሸጋገሩበት የታሪኩ ሁለተኛ ክፍል ጅማሬ ድረስ ታሪካቸው ያለአንቱታ እንዲቀርብ ተደርጓል:: ይህ አይነቱ ገለጻም ታሪኩ በምልሰት መሰል ዘመናትን በሚያነሳባቸው ስፍራዎች ሁሉ ተደጋግሟል:: ስለሆነም አንባቢያን ባለ ታሪኩ በጥቂት ገጾች ልዩነት ውስጥ በእርሱ እና በእርሳቸው የአክብሮት ገለጻ ሲጠቀሱ ግራ እንዳይጋቡ ለማስታወስ እንወዳለን:: ይህ አይነቱ የሦስተኛ መደብ ገለጻ ለታሪኩ አንዳች ኪናዊ ውበት የማጎናጸፍ ዓላማ ሲባል ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በመጽሐፉ ምዕራፎች መግቢያ እና አልፎ አልፎ እንደሚያስፈልጉ በታመነባቸው ቦታዎች ላይ ገብቷል:: ይሁንና አብዛኛው እና ዋናው የመጽሐፉ ክፍል በአንደኛ መደብ (ከባለታሪኩ አንደበት እንደሚቀርብ ሆኖ) ስለተተረከ አንባቢያንን ግራ አያጋባም ተብሎ ታምኖበታል:: በዚህ መልኩ ትረካው እንዲቀርብ የተደረገበት ምክንያትም ለትረካው ከሚሰጠው ሥነ ጽሑፋዊ ውበት ባሻገር አንዳንድ በወንጌላዊው የተተረኩ ትረካዎች ባለታሪኩ እኔ እያሉ ቢተርኳቸው ከሚፈጥሩ ስሜት

በላቀ ትረካውን በሦተኛ መደብ ተራኪ ድምጽ ማቅረቡ በአንባቢያን ምናብ የተሻለ ምስል የሚከስት አውድ ለመፍጠር ነው፡፡

ይህ ግለ ታሪክ (autobiography) ወንጌላዊ ኬዳሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ አምነውበት እና ለቤተክርስቲያን እንደሚጠቅም ታስቦ የተዘጋጀ ስለሆነ ወንጌላዊው ባለፉባቸው የተለያዩ የህይወት ምዕራፎች የሚፈጠሩ አከራካሪ ሁኔታዎችን በክስተቶቹ ውስጥ ድርሻ የነበራቸውን ወገኖች ላለመጥቀስ ብሎም በወንጌላዊው የአገልግሎት ድጋፍ የተደረገላቸው ወገኖችን በአሉታዊ መልኩ ገመናቸውን በሚያሳይ መልኩ ላለመተረክ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከተደረገው የላቀ ጥረት ባለፈ ስማቸው በመጽሐፉ ውስጥ በአሉታዊ መልኩ ተጠቅሶ የተገኙ ሰዎች ካሉ አስቀድመን ይቅርታ ለመጠየቅ እንወዳለን፡፡

አስቀድሞ እንደተጠቀሰውም ታሪኩ ሙሉ በሙሉ በወንጌላዊው ተተርኮ ከዚያም በብዙ ልፋት ሙሉ ዕርማት ያደረጉበት ስለሆነ በዚህ ታሪክ ውስጥ የተገለጹ ሃሳቦች በአጠቃላይ በወንጌላዊ ኬዳሞ የተነገሩ ወይም የወንጌላዊውን ሙሉ ይሁንታ ያገኙ ናቸው፡፡ ስለሆነም በታሪኩ ውስጥ የቀረቡ መረጃዎች በጥልቅ ምርምር የተገኙ ውጤቶች ሳይሆኑ የወንጌላዊ ኬዳሞ ብሩህ አእምሮ ለዘመናት ሰንቆ የያዛቸው ትውስታዎች ትረካዎች እንደሆኑ ልብ ይሏል፡፡ መጽሐፉ ከሚኖረው ኪነ ጥበባዊ ውበት በላቀ የላቀ መንፈሳዊ መልዕክት ማስተላለፉ የባለ ታሪኩም ሆነ የአዘጋጁ መሻት ነው፡፡ ስለሆነም በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ ታሪኮች በአጠቃላይ እውነተኛ መረጃዎችን ከማስተላለፍ እና በተመሳሳይ የህይወት መንገድ የሚጓዙ ሰዎችን ከማስተማር አንጻር የቀረቡ ናቸው፡፡

# የኔ ታሪክ አይደለም

እኔ እራሴን ባለ ታሪክ አድርጌ እና ባለታሪክ ሆኜ የራሴን ታሪክ ለመጻፍ ፈጽሞ ሃሳብ አልነበረኝም። ባለፉት ዓመታትም ብዙ ሰዎች በተደጋጋሚ ወደ እኔ መጥተው "ለምን ታሪክህን አትጽፍም?" ወይም "ታሪክህን እንጻፍልህ!" ብለውኛል። እኔ ግን የኔን ታሪክ ልጻፍ የሚል ፍላጎት አልነበረኝም። ደግሞም "የእኔ ታሪክ ቢጻፍስ ምን አስደናቂ ነገር ይኖረዋል?" ብዬ አስብም ነበር። በኋላም በአብርሃም ሕይወት የሠራውን፤ በአብርሃም ሕይወት ጣልቃ ገብቶ ያደረገውን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አስታወሰኝ። ልክ እንደ አብርሃም በኔ ሕይወት ጣልቃ ገብቶ ሁሉን የሠራው እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር በአብርሃም ሕይወት እንዳደረገው በመጀመሪያ ጠራኝ፤ በታሪኬ ውስጥ የእግዚአብሔር ጥሪ የነገሮች ሁሉ መጀመሪያ ነው። ከዚያም መቼም ላይተወኝ እስከ መጨረሻው የራሱ ሊያደርገኝ ቃል ኪዳኑን ሰጠኝ። እናም በዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ እርሱ የሰጠው ታላቅ ተስፋ አለ፤ እንድሸከመው አደራ ብሎ የሰጠኝ ዓላማም አለ፤ ያንን ለመፈጸም የሚያስችልም ከእርሱ የተሰጠ ኃይል አብሮኝ አለ፤ በዚህ ብቻ ሳያበቃም በእያንዳንዷ እርምጃዬ እርሱ የሚሰጠው አመራር አብሮኝ ነበረ። የሰጠኝ ተልዕኮ እና ተልዕኮውን የማስፈጽምበት የአፈጻጸም ስልት ሁሉ ከእርሱ ተሰጠኝ። ከዚያም ደግሞ የሚገኘው ውጤት ባለቤት እራሱ ነበር።

በእነዚህ ሁሉ የአገልግሎት ዓመታት እግዚአብሔር አንድም ጊዜ ከእኔ አልተለየም። ስስት መልሶኛል፤ ስደክም ኃይል ሰጥቶ አበርትቶኛል፤ ሳዝን አጽናንቶኛል፤ በማልፍባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ ከእኔ ጋር ሆኖ አሳልፎኛል፤ ከባድ ፈተና ውስጥ ስገባ መውጫውን አዘጋጅቶልኛል፤ ሁል ጊዜ አዲስ ኃይል እና አዲስ ፍቅር እየሰጠ እስከዛሬ አንቀሳቅሶኛል። በቆምኩበት ሁሉ መልዕክት ሰጥቶኛል። ከዚህ የተነሳ አንድም ቀን አልሰብክም ብዬ አላውቅም። እንደውም የት ሄጄ ልሰበክ የት ሄጄ ልናገር እያልኩ በጉጉት ነበር የምኖረው።

ሁል ጊዜ በኔ ለመጠቀም አላፈረብኝም፤ ሁል ጊዜ ረዳኝ፤ ሁል ጊዜ አበረታኝ፤ ታዲያ ይህ ታሪክ የማን ነው? ክብር ለእርሱ ይሁን! አሜን።


እግዚአብሔር ይህንን ታሪክ በኔ ሕይወት ሠራ። ደግሞም ለእናንተ እነግረው ዘንድ የዛሬ 66 ዓመት በ1942 ዓ.ም ጌታን ካመንኩበት ዕለት ጀምሮ ያለው የሕይወቴ ታሪክ ልክ ዛሬ ጠዋት እንደሆነ ሁሉ በአዕምሮዬ ታትሞ ቀርቷል። በ1943 ዓ.ም መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመግባት በነበረኝ ጉጉት የተጨነቅሁት ጭንቀት፤ በ1944 ዓ.ም ራሴን ሙሉ በሙሉ ለጌታ አገልግሎት ስሰጥ የተሰማኝ ደስታ ልክ ትናንት እንደሆነ ሁሉ ዛሬም ይሰማኛል። የመጀመሪያ ስብከቱን ስሰብክ፤ የመጀመሪያውን የወንጌል

ስምሪት ተቀብዬ ስወጣ፣ በየምዕራፉ የወደቅሁትን ውድቀት እና እግዚአብሔር የሰጠኝ ድሎች አንድ በአንድ በልቤ ማህደር በቅደም ተከተል ተቀምጠው እስከዛሬ ቆይተዋል። እግዚአብሔር ራሱ በእኔ ሕይወት የሠራውን ታሪክ ዛሬ ማስተላለፍ እችል ዘንድ ሳይደበዝዝ ትኩስ እንደሆነ እንዲቆይ አደረገው።

ስለሆነም የወንጌል አገልጋዮች ሁላችሁ እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ተጠቅሞ እንዴት እንደሚሠራ ትማሩበት ዘንድ ይህንን ታሪክ ተረክሁላችሁ።

ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ

# ክፍል ፩



# ምዕራፍ ፭

# በሻሾን የተተከለው ችግኝ

*“ምድር ያላችሁ ሁሉ ለእግዚአብሐር እልል በሉ... ኑ የእግዚአብሔርን ሥራ እዩ ከሰው ልጆች ይልቅ በምክር ግሩም ነው።” (መዝ (65)፡5)*

*ወቅቱ ለወንጌላውያን አማኝ ክርስቲያኖች የማይመች፣ የኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግሥት ሥልጣን የያዘበት ዘመን ነበር። ጊዜው ምንም እንኳን ከቤቱ የወጣ ለመመለሱ እርግጠኛ የማይሆንበት፣ ወጣቶች በየመንገዱ ዳር በጥይት የሚደፉበትና የተቀበሉው ሹማምንትና አብዮት ጠባቂዎች የሰው ልጅን ቁምስቅል የሚያሳዩበት፣ ቤተ ክርስቲያናትም በየጊዜው ይዘጉበት ከነበረው አስከፊ ጊዜ የተሻሻለ ቢሆንም አሁንም ግን የወንጌል አማኝ መሆን ብቻ በራሱ እንደጥፋት የሚታይበት ወቅት ነበር።*

*ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ በመሪ ወንጌላዊነት ከሚያገለግሉባት በአዲስ አበባ ቀደምቷ እና ትልቋ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን (መሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን) ፎልስ ዋገን መኪናቸውን እያንዶቀዶቁ መካኒሳ አቅራቢያ ቫቲካን ኤምባሲ አካባቢ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው እየገሰገሱ ነበር። በዚህ ዕለትም ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት ሙሉ ሱፋቸውን ግጥም አድርገው ለብሰው እና ከአለባበሳቸው ጋር የሚሄደውና ሁልጊዜም የማይለያቸው ቆፍጠን ያለ ገጽታቸው አብሯቸው ነበር። ወደ ቤታቸው አቅራቢያ ሊደርሱም የቫቲካን ኤምባሲን አጥር ታክኮ በሚሄደው ቀጭን መንገድ ታጥፈው ወደ ቤታቸው የሚወስደውን ዳገት ሽቅብ ይወጡ ጀመር። ከዚያም በኮረኮንች የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ፎልስ ዋገኗ ተሽሎክሉካ ገባች እና ወንጌላዊው ቤታቸው ደጃፍ ደረሱ። የመኪናቸውን ጥሩምባ አስሰምተው የጊቢው በር ከተከፈተ በኋላ መኪናቸውን በተለመደው የማቆሚያ ሥፍራ አቆሙ። ከመኪናቸው ወርደው ግርማ ሞገስ ያጎናጸፏቸውን ሙሉ ልብሳቸውን እንደለበሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መያዣ ቦርሳቸውን አንጠልጥለው ወደ ውስጥ ዘለቁ።*

*ወንጌላዊ ኬዳሞ ገና ወደ ቤቱ ሳሎን ሲገቡ በቤት የነበሩት ልጆቻቸው፣ ባለቤታቸውና ሊጠይቋቸው ከገጠር የመጡት እናታቸው “ነምር” ብለው ተነሱ። በዚህ ጊዜ የወንጌላዊ ኬዳሞ እናት ወ/ሮ ሺቢቤ አፋቸውን በመገረም ይዘው “ጉድ ... ጉድ ... ጉድ ...*

አሁን በሆድ ውስጥ ሞቶ ከዛሬ ነገ ጭንጋፉ ይወጣል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረ ሽል ነፍስ ዘርቶ ተወልዶ አድጎ እንዲህ የተከበረ ሰው ሆኖ ማየት ይገርማል።" አሉ።

ለነገሩ ወ/ሮ ሺቢቤ ኬዳሞ ልጅ እያለ ጀምሮ ሲያበሳጯቸው «ያኔ ፈርሶ የነበረው ጽንስ እያለ ምነው ፈርሶ በቀረ!» ይሉ ነበር። ሲያስደስቷቸው ደግሞ «ልትጠፋ የነበርክ ልጅ እንዲህ አድገህ አስደሰትከኝ!» እያሉ ይገረማሉ። ይህን የሚሉበት ምክንያትም ወ/ዊ ኬዳሞ በተጸነሱበት ጊዜ ጽንሱ ገና ሳይጠነክር በሆዳቸው ውስጥ ሞቶ ለወራት ከሆድ ሳይወጣ ሳይንቀሳቀስ ቆይቶ ከዚያ በኋላ እንደገና ነፍስ ዘርቶ ስለ ተንቀሳቀሰ ነበር ከመወለጃ ጊዜው በጣም የዘገየ ወንድ ልጅ የተወለደው። ስለዚህም ኬዳሞ የተወለዱባትን የሻሾን ገጠራማ መንደር ላየና የህጻንነት ወራታቸውን ለተመለከተ ዛሬ የወ/ዊ ኬዳሞን የተስተካከለ ቁመና በላያቸው ልክክ ካለው ሙሉ ልብስ ጋር ለሚያያቸው፤ የቤተሰባቸውን፣ የመኖሪያ ቤታቸውንና ከሁሉም በላይ ታላቁን የአገልግሎታቸውን ስኬት እና ብዙ ውጤታማ የወንጌል ስብከት ዘመናቸውን ያስተዋለ ሰው እዚህ መድረሳቸው ያስገርመዋል።

ወንጌላዊ ኬዳሞ የተወለደው በአሁኑ አጠራር በደቡብ ሕዝቦች ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ውስጥ በሚገኘው ሃዲያ ዞን ሻሾን ወረዳ ውስጥ ነው። ሃዲያ ዞን በዚሁ መጠሪያ የሚጠሩት እና ከኩሽቲክ ቋንቋዎች አንዱ የሆነው ሃዲይኛ ተናጋሪ ሕዝቦች መገኛ ነው። የሃዲያ ግዛት ስም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ይነሳ የነበረ ሲሆን ከማዕከላዊው ስርወ መንግስት ጋርም በገባር አልገባርም ጦርነት ሲያደርግ የኖረ እና እልፍ ሲልም በዘመኑ በነበረው ልማድ መሰረት ሰላም እና ወዳጅነት ለመፍጠር በማሰብ የማዕከላዊው አገር ንጉስ ከሃዲያ ንጉስ ልጅ ጋር ተጋብቶ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። ይህቺው የሃዲያ ንጉስ ልጅ የሆነች ንግስትም (ንግስት እሌኒ የተባለችው) የስመ ጥሩ ንጉስ ዘርአ ያዕቆብ ሚስት እንደነበረች እና ስሟም ከንጉሱ እኩል መጠራት የቻለ እቴጌ እንደሆነች ይነገራል።

ሃዲያዎች በአቅራቢያቸው ካሉት የከምባታ፣ የጉራጌ፣ የስልጤና የኦሮሞ ሕዝቦች ጋር በልዩ ልዩ መልክ ተመሳሳይነት ያለው ባህል ያላቸው ሕዝቦች ሲሆኑ ዘለግ ያለ ቁመናቸው እና ጠየም ያለ መልካቸው ከተቀረው የኩሽቲክ ቋንቋ ተናጋሪ ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያመሳስላቸዋል። የሃዲያ ግዛት እስከ የኦሮሞ ሕዝብ መስፋፋት ዘመን ድረስ ሰፊ የድንበር ወሰን ያካልል የነበረ እና በጦረኝነቱ ይታወቅ የነበረ ሕዝብ ሲሆን ሃዲያዎች ከተተከለ ለመንቀል አስቸጋሪ የሆነው ባለ ድርብ ስለት ጦራቸው መለያቸው ነው።

ኬዳሞም በዘመዶቻቸው መካከል ጦረኛ በሚወደስበት ባህል ውስጥ አድገው ራሳቸው ጦረኛ ሲሆኑ፣ ሲሸፍቱ፣ ሲገድሉ እያደገደጉ በነበረበት ወቅት እግዚአብሔር ደርሶ የሕይወት አቅጣጫቸውን አስቀይሮ የወንጌል አርበኛ አደረጋቸው። ይህ አስደናቂ ታሪክም እንዲህ ይጀምራል።

# የተገኘሁበት ማኅበረሰብ

የተወለድኩት ከሁለት ብሔረሰብ ከተገኙ ወላጆቼ ነው። አባቴ ከሃዲያ ብሔረሰብ ሌሞ ጎሳ የተገኙ ሲሆን የመኖሪያ መንደራቸው ቃልሼ የመጠሪያ ስማቸውም ሚቻቶ ሄሴ ኩሌሎ ይባላል። የአባቴ እናት የተገኙትም ከዚያው ከሃዲያ ብሔረሰብ ሆኖ ሻሾጎ ውስጥ ቢዲቃ አሼኤ ከሚሰኝ ጎሳ ነው። ሴት አያቴ ስማቸው ሃሲሴ ሌጋሞ ይባላል። እናቴ ደግሞ ከከንባታ ብሔረሰብ ያንገር ጎሳ የተገኙ ሲሆን የመኖሪያ ስፍራቸው አበላ ይባል ነበር። እናቴ ወ/ሮ ሺቢቤ ሊረሞ ይባላሉ። እናታቸውም (ሴት አያቴ ማለት ነው) በደመና ከሚባል የከንባታ ዘር የተገኙ ሲሆን ወ/ሮ ሊባቤ ወናሴ ነበር ስማቸው።

ከላይ ስማቸውን የጠቀስኳቸው የዘር ግንዶቼ በሙሉ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ እንደሚያደርገው በግብርና የሚተዳደሩ ሰዎች ነበሩ። ስለሆነም እንደ በጎች፣ ፍየሎችና የጋማ ከብት የሆኑትን እንደ በቅሎ፣ ፈረስና አህያ የቤት እንስሳትን የመሳሰሉ እያረቡ፤ እርሻ እርሰው በቆሎ፣ ማሽላ፣ ገብስ፣ ስንዴና ጤፍ እያመረቱና እንሰት ተክለው በመፋቅ ቆጮ እያመረቱ ኑሮአቸውን ይመሩ ነበር። በአካባቢያችን ሁሉም ሰው የራሱን ኑሮ ራሱን ችሎ ይመራል፤ እንዲመራም ይጠበቅበታል። አልሠራም ብሎ የሰነፈን ሰው የቤተ ዘመድ መሪዎች በጎረምሶች ያስደበድቡታል። በወቅቱ እነዚህ አንድ ወገን የሆኑ ሕዝቦች በየጎሳቸውና በየመንደራቸው እየተረዳዱና በሁሉ እየተጋገዙ በግልም እየሠሩ ለዕለት ኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን እያሟሉ ይኖራሉ። ወላጆች ልጅ ወልደው ሲድሩም ለልጆቻቸው (ሴትም ሆነ ወንድ) እንደየአቅማቸው ከብትም ሆነ የእርሻ መሬት ይሰጣሉ።

ኅብረተሰቡ ራሱን የሚያስተዳድረው በከምባታም ሆነ በሃዲያ መሪነት ከቤተሰብ ጀምሮ ወደ ቤተ ዘመድና ጎሳ ይሄድና በየወገኑ የተመረጡ መሪዎች ማንኛውንም ችግር ይፈታሉ፤ የተጣሉትን ይዳኛሉ። የአካባቢው ገዢ የሆኑት የመንግሥት ባላባቶች የመንግሥትን ግብር ከመሰብሰብና ከማስገበር ውጪ በዚህ ዓይነቱ የጎሳ አመራር ላይ ፈጽሞ ጣልቃ አይገቡም ነበር።

በዚያ ዘመን የነበረው ዋና አስከፊ ነገር ሕዝቡ በሰይጣን አምልኮ የተተበተበ ስለነበር የኔም ወገኖች በእናቴም ሆነ በአባቴ በኩል ለሰይጣን ተመሳሳይ አምልኮ ያደርጉ ነበር። የአምልኮ ዓይነቱም ለወንድና ለሴት ይለያያል። ሴቶቻችንን የሚመራው ሰይጣን "ኢዶታ" ሲባል እርሱን የሚመራው ዛር ደግሞ "ወሬቆ" ተብሎ ይጠራል። "ወሬቆ" ማለት "የሚያቀጭጭ ወገ" ማለት ነው። ወንዶች የሚያመልኩት ሰይጣን ደግሞ "ጃራ" ይባላል። የጃራን አምልኮ የሚመራው ደግሞ "ሱዶ" የሚባል ዛር ሲሆን ትርጓሜውም "ወገ" ማለት ነው። በዚህ በሱዶ መሪነትም ሁላችንም ሰዎችን፣ አራዊትን፣ እንስሳትን፤ አሞራና ወፎችን፣ ዛፎችንና ሣር ቅጠሉን ከማምለክ አልፈን ሞቶ የተቀበረ ሰው መቃብርን የምናመልክ ሕዝቦች ነበርን። ለምሳሌ፦ ከአራዊቶች መካከል ጅብ ስለሚመስክ ጅብ ወደ መንደራችን ሲመጣ እናቴና ሌሎች ተቀብለው

በረጅም የቀንድ ማንኪያ ቅቤ ሲያጎርሱት ገና ታዳጊ ሳለሁ በዐይኔ አይቻለሁ። ደግሞም በግ ወይም ፍየል አርደው ምግብ ያዘጋጁና ያዘጋጁትን ወደ ወንዝ ወርደው ለጅብ ይሰጡ ነበር። መንገድ ሊሄዱ የወጡ ሰዎች የወፍ ድምጽ ከኋላ ሲሰሙ ችግር አለ ብለው ይመለሱ የነበረ ሲሆን ከፊት ወፍ ከጮኸ ግን "አምላካችን ከፊት ሆኖ ጮኸ ስለዚህ መንገዱ ጥሩ ነው" ብለው ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ።

ከዚህም አልፎ ደግሞ ለጨረቃና ለፀሐይ ይሰገዳል። ጨረቃ በምትወጣበት ወቅት ለመጀመሪያ ስትታይ ወንድና ሴቱ ሁሉ እጁን ዘርግቶ አምልኮ ያካሄዳል። ጨረቃን ‹‹አንተ የኖርከውን ያህል ዘመን እኔንም አኑረኝ›› እያለ ይማጸናል። ወደ አስር ሰዓት ሲሆን ደግሞ ለፀሐይቱ አይብ ያዘጋጁና በላዩ ላይ ቅቤ ጨምረው ሌላም ልዩ ልዩ ምግብ አዘጋጅተው ያንን ጮጮ ክዳን ላይ ያደርጉና ቅቤውን ሥጋና በሚባል ሣር እያጠቀሱ ወደ ፀሐይ ይረጫሉ። ‹‹አንተ ብርሃን ሁን›› እያሉም ስግደት ያካሄዳሉ። በእውነቱ በወቅቱ የነበርንበት ሁኔታ በዚህ መሰሉ የሰይጣን አሰራር ተተብትበን መሄጃ ያጣንበት የጨለማ ሕይወት ነበር።

ከዚህ ሁሉ አምልኮ ጋር ከየትኛው ወገን እንደሚመደብ የማይታወቅ ሃይማኖትም ነበረን። ይህ ሃይማኖታችን "ፊንዳኖ" ይባል ነበር። በዚህ ኃይማኖት ሳለን በዓመት ለሁለት ሳምንት ቀን ቀን እንፆም ነበር። ፆሙ የሚፆመው ወንዶች በማለዳ ተነስተው ወንዝ ይወርዱና ታጥበው ጥፍራቸውን ቆርጠው፣ ኃጢአታቸውን ተናዝዘው ሲመለሱ "ሶመን ሃቃ" ከሚባል የፆም ዛፍ ላይ አበባ ቆርጠው ሌላ ሌላም ሣርና ቅጠላ ቅጠል ጨማምረው "ሐይቦ ሐይቦ" እያሉ እየዘመሩ ሲመጡ ቤት ውስጥ ያሉ ሴቶችም ወንዶቹን በእልልታ ይቀበላሉ።

እንግዲህ ይህን በመሰለ የጨለማ ሕይወት ተተብትበን ባለንበት ጊዜ ነው እኔ የተወለድኩት።

## ቤተሰቤ

ወላጅ አባቴ ከእናቴ በፊት ከነበሩአቸው ሚስታቸው የወለዷቸውን ጨምሮ እኔ የተወለድኩት ስድስተኛ ልጅ ሆኜ ነው። አባቴ በመጠኑ ሃብት የነበራቸው ትጉህ ሠራተኛና ኃይለኛ ሰው ነበሩ። በልጅነቴ እንደማስታውሰው ከ80-90 የሚሆኑ ላሞችና ከ70-80 የሚሆኑ በግና ፍየሎች፣ ብዙ አህዮች፣ ፈረሶችና በቅሎዎችም እንዲሁም በገንዘብ የተገዙ ባሪያዎችም ነበሩአቸው። እኔ በአጠቃላይ ሦስት ወንድሞችና አራት እህቶች ነበሩኝ።

አባቴ በጣም ቁጡ ሰው ስለ ነበሩ ከዚህ ባህሪያቸው የተነሳም ሰዉና ከብቱ ሣይቀር ፈርቶአቸው ይኖሩ ነበር። በአንጻሩ እናቴ ደግሞ ጭምት ታጋሽና ብልህ ሴት ነበሩ። አንዳንድ ጊዜ አባቴ እናቴን በኃይል ደብድበው ሲያበቁ ቅርብ ወደነበረው የእናቴ ወላጆች ቤት አድርሰው ይመለሱ ነበር። በሀገሩ ልማድ ብዙ ሴቶች ተደብድበው ወደ

ወላጆቻቸው ቤት ሲወሰዱ ሽማግሌ ይዘው ይመለሱ የነበረ ቢሆንም እናቴ ግን ይህን አያደርጉም ነበር። ይልቁንም ቤታቸውንና ልጆቻቸውን በጣም ስለሚወዱ ደግሞም በጣም ታጋሽ ስለነበሩ ወዲያውኑ ከአባታቸው ቤት ተመልሰው በዚያው ዕለት ምግብ ያዘጋጁና ለሠራተኞች ሰጥተው ይደበቃሉ። መሽቶ አባቴ ከተኙ በኋላም ሄደው አጠገባቸው ይተኛሉ።

ከዚህ ኃይለኛ ባህሪያቸው የተነሳ አባቴ በቤተሰቡ ሁሉ በጣም የሚፈሩ ሲሆን በቤታችን ሁልጊዜ ቀጣና ፍርኃት ነግሶ እንኖር ነበር። እኔም ገና በልጅነቴ በዚህ በአባቴ ባህርይ አዝን ስለነበር "ሀገር ሰላም እያለ ለምን ሁል ጊዜ በቤታችን ሽብር ይሆናል?" እያልኩ እማረር ነበር። ከዚህም የተነሳ "እኔ ትዳር ከያዝኩ ባለቤቴንም ሆነ ልጆቼንም ሳያጠፉ አልቆጣም! በሰላም ሁሌ ተደስቼና ስቂ እኖራለሁ።" ብዬ ገና በልጅነቴ መወሰኔን አስታውሳለሁ።

አባቴ ምንም እንኳን በጣም ቁጡና ኃይለኛ ቢሆኑም ቤተሰብ በማስተዳደር በኩል ግን የተዋጣላቸው ነበሩ። በሥራ በኩል የከብት እርባታንም ሆነ የእርሻ ሥራን ቀጥ አድርገው ያስተዳድሩ ነበር። ለምሳሌ፦ የኛ ቤት ልጆች (የኔ ታላላቆች) እንደ አካባቢው ባህል ወደ ዘፈን ቦታ አይሄዱም ነበር። እህቶቼ አንድ ቀን እንኳን ሠርግ ሳይሄዱ የተዳሩ ሲሆን ታላላቅ ወንድሞቼም ዘፈን ያለበት ቦታም ሆነ ወደ ጨዋታ ሄደው አያውቁም ነበር። አንዳንዶቹማ ገበያ እንኳን ሳይላኩ ነው ተድረው ከቤት የወጡት። አባቴ ከኃይለኝነታቸው የተነሳ ማንኛውንም የቤተሰብ አባል ተጣርተው ሳይራገሙ ወይም ሳይሳደቡ በሰላም አያናግሩም። ይህ ቁጣቸው ደግሞ ከኛ አልፎ ለቤት ሠራተኞችም ይተርፋል። የአባቴ ሞገደኛ ባህርይ በመንደራችንም የታወቀ ነበር። በዘመኑ ይደረግ እንደነበረው በገንዘብ የተገዙ ሁለት ወንድ እና ሴት ባሪያዎች ነበሩን። በዚያ ዘመን ባሪያዎችን በገንዘብ ገዝቶ ክቡር የሰው ልጅን እንደ ሸቀጥ ንብረት ማድረግ ከአገራችን ገና ያልተወገደ ልማድ ነበር። ስለሆነም አባቴ እንደራሳቸው ንብረት የሚቆጥሯቸው ባሪያዎች እንዲጋቡ ሲወስኑ ሴቷ እንቢ ብላ አስቸገረች። ይሁንና በኋላ አባቴ በግድ ደብድበው አጋብተዋቸዋል።

አባቴን ከዚህ ቁጡ ባህሪያቸው የተነሳ የአካባቢው ሕዝብ እንኳን ይፈሩአቸው ነበር። ስለዚህም ሰዎች በዘፈን ቅኔ አስደግፈው የአባቴን ኃይለኝነት ይገልጹ ነበር። አንድ ጊዜ የኔ የታናሽ ታናሽ የሆነው የአባቴ ስምንተኛ ልጅ ሞተ። አባቴ ደግሞ ለቅሶ ተቀምጠው መጽናናትና የእዝን ንፍሮ መብላት አይወዱም። ስለዚህ የአካባቢው ሰው እድማ አደረገ። ከቀብር በኋላ እህል አምጥተው ንፍሮም ቀቅለው ካቀረቡ በኋላ "እርሱ ሰው ቤት ስለማይበላ እኛም እርሱ ቤት አንበላም።›› ብለው ለብዙ ሰው የተዘጋጀውን ንፍሮ ንክች ሳያደርጉ አስቀምጠው ሄዱ። አባቴም ‹‹የራሳችሁ ጉዳይ! እናንተ ባትበሉ ላሞቼ ይበሉታል!›› ብለው ነገሩ ምንም ሳይመስላቸው እንደዋዛ አልፈውታል።

ይህን ሁሉ የአባቴን ኃይለኝነት የዘረዘርኩት ገና በሕፃንነቴ የነበረው የቤተሰባችን ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበር ለማሳየት ነው።

እናቴ ወ/ሮ ሺቢቤ ደግሞ ጭምት ከመሆናቸው ባሻገር በጣም አስተዋይ እና ጥበበኛ ሴት ነበሩ። የእናቴ ጥበበኝነት የሚጀምረው ገና ከታዳጊነታቸው ነው። እንደውም እኔ ዛሬ እዚህ ለመድረሴ ምክንያት ከሆኑት እና ነገሮችን በትጋት እና በጥበብ እንዳከናውን ካስቻሉኝ እግዚአብሔር አስቀድሞ ወደ ሕይወቴ ያመጣቸው መልካም እድሎች መካከል የእናቴ ትጉህ እና አስተዋይ ማንነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።

እናቴ ባደጉበት በአባታቸው ቤት አባታቸው ባለ ብዙ የንብ ቀፎ ነበሩ። እናቴ ገና ከታዳጊ የልጃገረድነት እድሜያቸው ጀምሮ በዚህ የንብ እርባታ እና የማር ማምረት ሥራ ውስጥ  ይሳተፉ ነበር። በንቦች የአኗኗር ሥርዓት መሠረት አውራው ንብ በአንድ የንብ ቀፎ ውስጥ አንድ ዓመት ቆይቶ ቀፎውን ትቶ ለመሄድ ይፈልጋል። በዚህ ጊዜ አውራ ንቡ ሌሎችን የንብ መንጋዎች አስከትሎ ከቀፎ ይወጣ እና በአቅራቢያው ባለ ዛፍ ላይ ያርፋል። አውራ ንቡ መንጋውን አስከትሎ ከሄደ ስለማይመለስ እናቴ በጥበብ አውራውን ብቻ ነጥለው ይይዙታል። ከዚያም አዲስ ቀፎ ውስጥ ይከቱታል። የንብ መንጋዎቹም አውራውን ተከትለው አዲሱን ቀፎ ይሞሉታል። በዚህ ዓይነት የንብ እርባታው ውጤት እንዲያስገኝ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።

ማር በሚቆረጥምበት ወቅት እናቴ እንዲበሉ የሚሰጣቸውን ማር መብላት ትተው ያጠራቅሙ እና ይሸጡታል። በዚህ መንገድ ባጠራቀሙት ገንዘብ ጊደሮች ገዝተው የራሳቸውን ከብቶች ያረቡ ነበር። ከአባቴ ጋር ከተጋቡ በኋላም እናቴ የራሳቸው የሆኑ ከብቶች ነበሯቸው። አባቴ ሞተው እኛ ካደግን በኋላ ከዚያም አልፎ አርጅተውም እንኳን ሳይቀር የራሳቸው ከብቶች ስለነበሯቸው እድሜ ልካቸውን የእኛን እጅ ሳይጠብቁ ነበር የኖሩት። እናቴ በሞቱበት ጊዜም ከብቶቻቸውን ለኔ እና ለወንድሜ ፈይሳ ልጆች ነበር ያወረሱት።

ሌላው የእናቴን ብልህነት የሚያሳይ አጋጣሚ ደግሞ እኔ ገና በጣም ትንሽ ልጅ እያለሁ ጣሊያን አገራችን ሲገባ ነበር የተፈጠረው። ጣሊያን አገራችንን በወረረ ጊዜ በምድር የነበረውን ጦርነት የጠብመንጃ እና የመድፍ ጥይት ሽሽት ብሎም ከሰማይ በዚያ ዘመን (በተለይ ለገጠሩ የአገራችን ሕዝብ) እንደ የአምላክ ቁጣ የታየውን የአውሮፕላን ድብደባ ለማምለጥ ሕዝቡ ሁሉ ቤቱን ጥሎ ይሸሽ ነበር። እኛም ጦርነቱ በአካባቢያችን ተካሂዶ አሸናፊ እና ተሸናፊው እስኪለይ ቤታችንን ጥለን ሸሽተን ነበር። ሆኖም ያኔ ሰው ሁሉ ማቄን ጨርቄን ሳይል በሚሸሽበት ጊዜ የኛ እናት አስቀድመው በደንብ ተዘጋጅተው ነበር እኛ ቤታችንን ጥለን የሸሸነው። በመጀመሪያ በሽሽት ወቅት የምንበላውን ስንቅ በሁለት አህዮች ላይ (በአንዱ ላይ ብስል፣ በአንዱ ላይ ጥሬ እህል) አዘጋጅተው በቁርበት ስልቻ ሞልተው ጭነው ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እናታችን አስቀድመው በጎተራ የነበረንን እህል በሙሉ እንዳይታይ አድርገው በአራት ቦታ (በከብቶች በረት እና በቤታችን በልዩ ልዩ ቦታዎች) ባስቆፈሩት ጉድጓድ ውስጥ ከቀበሩ በኋላ ነበር መንደራችንን ለቅቀን የጠፋነው።

ጦርነቱ ጋብ ካለ በኋላ ወደ መንደራችን ስንመለስ የኛ መንደር ሳይቃጠል ነበር ያገኘነው። ሆኖም ሰው ወደ ቀድሞ ኑሮው ተመልሶ እርሻ ማረስ ሲጀምር ሌላው ሕዝብ እህል ደርሶ የሚበላው እስኪያገኝ ብዙ ተቸገረ። እኛ ግን እናቴ አስቀድመው ቆፍረው የቀበሩትን እህል ማታ ማታ እያወጣን እየበላን ከኛም አልፈን ለቅርብ ዘመዶቻችን ሁሉ ተርፈን ጊዜውን ያለ ችግር አሳለፍን።

እናቴ ወ/ሮ ሺበቤ ከዚህም ባለፈ በጣም አስተዋይ፣ ታጋሽ እና ትጉህ ሴት ሆነው ነበር እድሜያቸውን ሙሉ የኖሩት። እናቴ በኋለኛው የዕድሜ ዘመናቸው ክርስቶስን አምነው እርሱን እያመለኩ ነበር የኖሩት። እኚህ ትጉህ እናቴ እዕሜያቸው ከአንድ መቶ ዓመት በላይ ሆኖ እንኳን ሥራ ወዳድ ሆነው ኖረው ወደ ጌታ ሄደዋል። በቀብራቸው ላይ የሰበኩ ከተለያየ ቦታ የመጡ ሦስት አገልጋዮችም በምሳሌ መጽሐፍ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሰችውን ሴት ከእናቴ ጋር እያመሳሰሉ ተናግረዋል።

## ልጅነቴ

በሕፃንነቴ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሕፃን እረኛ ሆኜ ነበር ያደግሁት። በመጀመሪያ የጥጆች ከዚያም የፍየሎችና የበጎች ጠባቂ ሆንኩ። ትንሽ ከፍ ስልም ከብቶች መጠበቅ ጀመርኩ። ከልጅነቴ

ጀምሮ ማንኛውንም ሥራ በሚገባ የምሠራ ትጉህ ነበርኩ። ምንም እንኳን ዋና ሥራዬ እረኝነት የነበረ ቢሆንም ገና ትንሽ ልጅ እያለሁ ጀምሮ በርካታ ተያያዥ ሥራዎችን እሠራ ነበር። በተለይም በ8 ዓመቴ አካባቢ አንዲት ታላቅ እህቴ ባል አግብታ ስትሄድ የእርሷ አገልግሎት ስለቀመ ቤታችን ውስጥ ያለው በርካታ የመስክና የማጀት ሥራ ሁሉ በኔ ጫንቃ ላይ ወደቀ። ከከብቶች ቤት እበት የመጥረግ፣ ሣር የማጨድና እንጨት የመፍለጥ ኃላፊነት በኔ ላይ ቢጣልም ሁሉንም ምንም ሳይመስለኝ እሠራ ነበር።

ሁልጊዜ ወትር ማለዳ (12 ሰዓት ሳይሞላ) ተነስቼ ከብቶች ከበረት ወደ ሜዳ አስወጣለሁ። ከብቶቹ ሜዳ ላይ ተኝተው እያለም ለጥጆች ሣር አጭጄ አመጣለሁ። ከዚያም የነበሩን ብዙ ላሞች ይታለቡና እነርሱንና ሌሎች ከብቶችን እየነዳሁ ወደ ሜዳ ሄጄ ሳግድ እውላለሁ። በዚህ ብቻ ሳልወሰን የከብቶቻችን በረት ከቤታችን ይርቅ ስለነበረ ገና በታዳጊነቴ ጦሬን ይዤ እስከ ሌሊቱ 9 ሰዓት ከብቶችን ስጠብቅ አመሽ ነበር። በእናትም በአባትም የሚገናኘኝ ታላቅ ወንድሜ ኃይለኛ ሰው ቢሆንም ሥራ ላይ ግን የኔን ያህል ትጉህ አልነበረም። እኔ ከእርሱ ይልቅ ትጉህ ነበርኩኝ። ከዚሁ ከከብቶች ጥበቃ ጋር በተያያዘም ከብቶቻችን ባሉበት ስፍራ በየቀኑ የሚናጠውን ቅቤ ለየብቻ አስሬ አስቀምጣለሁ። እናቴ ወር ላይ መጥተው የ30 ቀን ቅቤ ለየብቻ ታስሮ በአንድ ገበታ ላይ ተቀምጦ ሲያዩ ተደስተው "ልጆችህ አንተንም እንዲሁ ያክብሩህ!" እያሉ ይመርቁኝ ነበር።

ሌላው አስደናቂ የልጅነት ባህርዬ ደግሞ ገና ትንሽ ልጅ እያለሁ በስድስት እና ሰባት ዓመቴ የምጫወተው ጨዋታ ከኔ የማይጠበቅ መሆኑ ነበር። በጊዜው በኛ ቤትም ሆነ በአካባቢያችን ማንም እንደ አሁኑ እጀ ጠባብና ኩታ ለብሶ አይታይም። እናቶቻችን በጊዜው ቁርበት ይለብሱ የነበረ ሲሆን አባቴ ብቻ ጥሩ ጥሩ እጀ ጠባብ፣ ኩታና ሱሪ ነበራቸው። ግን የእርሳቸውም ልብስ ቢሆን በጋን ውስጥ ታሽጎ ይቀመጥ ነበር እንጂ አይለበስም። ታዲያ እኔ ያኔ ምንም ባላየሁበት ዘመን እንጨት ሲፋቅ ተገልፍፎ የሚቀረውን ልጥ እና የእንሰት ነጩን የውስጠኛውን ክፍል ወስጄ እንደ አንሶላና ብርድ ልብስ ከላይና ከታች አንጥፌ እተኛለሁ። ደግሞም ወፍቾ እንደ ጫማ እግሬ ላይ አድርጌ እሄዳለሁ። አንዳንድ ጊዜም የወደቀ ባርኔጣ ምናምን ሳገኝ ጭንቅላቴ ላይ አድርጌ እመጣና የአማራ ባላባቶች ያደርጉ እንደነበረው ከጭንቅላቴ አንስቼ ጤና ይስጥልኝ ብዬ እገባለሁ።

ይህንን ሁሉ ሳደርግ ያዩት አባቴ "ይህ ልጅ ቢማር ጥሩ ነው። ከግራዝማች ዳድቼ ጋር አገናኘዋለሁ" ይሉ ነበር። ታላቅ ወንድሜ ያኔ ጨዋታ የሚጫወተው የከብቶች በረት እየሠራ እና በመሰል ተግባራት ነበር። እኔ ግን ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ የከባ ግንድ አጣምሜ በእርሱ ላይ አንድ ልጅ አስቀምጬ እጎትታለሁ፤ ከዚያም ልጁ እኔን ይጎትተኛል። ከባ በማጣበት ጊዜ ደግሞ ከጫካ እንጨት መዝገፍ እንደበትር አዘጋጅና በእርሱ ላይ እንጣጥ አንጣጥ እያልኩኝ እንደ ፈረስ ጋላቢ እሄድና ከዚያ ላይ ዘልዬ ወርጄ "ጤና ይስጥልኝ" እል ነበር። ይህን ሁሉ ነገር በጊዜው እኔ በዓይኔ አላየሁትም ነበር። ነገር ግን በጊዜው እንደ ትንቢት ሆኖ ዛሬ በሕይወቴ የተፈጸሙትን እነዚያን ነገሮች ሁሉ ማለትም በአልጋ ውስጥ አንሶላና ብርድ ልብስ ለብሶ መተኛትን፣ መኪና መንዳትን፣ ባርኔጣና ሙሉ ልብስ ማድረግን ያኔ እንደ ጨዋታ እሞክራቸው ነበር። ያኔ የከብቶች በረት እየሠራ ይጫወት የነበረው ታላቅ ወንድሜም እድሜ ልኩን ከብት አርቢ ሆኖ ኖሮ የከብቶች በረት ሲሠራ ሞተ።

እንዲህ እንዲህ እያልኩ ካደግሁ በኋላም ገና በታዳጊነቴ ታታሪ ሠራተኛ እና የቤተሰቦቼ አገልጋይ ሆንኩ። ትንሽ ከፍ እያልኩ ስሄድም ምንም እንኳን በጣም ትጉህ ሠራተኛ ብሆንም ከአባቴ የወረስኩት ኃይለኛነት በኔም ሕይወት ይታይ ጀመር። ይህን ኃይለኛነቴን ደግሞ አባቴ ላይ ሁሉ አሳይ ነበር። አባቴ በጣም ቁጡ የነበሩ ሲሆን በቤታችን እንደተለመደው ማንንም ሰው ሥራ ለማዘዝ ሲጣሩ "አቤት" ካሏቸው በኋላ ሳይሳደቡና ሳይራገሙ የፈለጉትን ነገር አይናገሩም። እኔ ግን ይህንን እርግማናቸውን በመቃወም ሊያዝዙኝ ፈልገው በቁጣ ሲጠሩኝ አልመልስላቸውም ነበር። ምክንያቱም እኔ "ምን የሚያስቆጣ ነገር መጣ? ከብቱ? ሰዉ ሁሉ ደህና ነው። በዚያ ላይ እኔ እንደዚያ እየለፋሁ በሰላም መጥተው 'ጎሽ!' እንደማለት ለምን ይቆጣሉ?" ብዬ አጉረመርማለሁ። ስለዚህም ሲጠሩኝ "አቤት" ካልኩ ስለሚራገሙ ዝም እላለሁ። እርሳቸውም ምላሽ ሲያጡ እኔን አሳድደው ዱላ ይወረውሩብኛል። ነገር ግን በጣም ፈጣን ስለነበር ሸሽቼ አመልጣለሁ። ይህ ዓይነቱ ነገር በተፈጠረ ቀን ከብቶቹን በረት

አስገባና እኔ ተመልሼ እደብቃለሁ። በኋላም በጣም ከጨለመ በኋላ ቀስ ብዬ ገብቼ ቆጥ ላይ ወጥቼ እተኛ ነበር።

ከነበረኝ ኃይለኛ ባህርይ የተነሳ በቤትም ሆነ በውጪ እኔን መያዝ የሚቻለው በፍቅርና በጸባይ ብቻ ነበር። እኔን የሚወዱኝ እና ስለኔ መልካም የሚናገሩ የሰፈር ሰዎችን ሰብል በገዛ ፈቃዴ እርማለሁ፤ ማሽላቸውን ወፍ እንዳይበላው በወንጭፍ እጠብቃለሁ፤ ሰብላቸውንም ከብት እንዳይበላ እጠብቃለሁ። ስለኔ መጥፎ የተናገረ ሰው ካለ ግን ሰብሉ ላይ ከብቶች እለቅቃለሁ፤ አንዳንዴ ከአልሽኝነቴ የተነሳ ሰዎች ሰብል ላይ ፍየሎች ለቅቄ ሰዎቹ ተበሳጭተው ፍየሎቹን ሲያስሩ ሁሉ እኔ ግን ግድ አይሰጠኝም አንዳንዴም ሰዎች ለአባቴ ሄደው ቢናገሩም እኔ ግን ፈጽሞ ከዚህ ተግባሬ አልመለስም ነበር።

ስለኔ መጥፎ የሚናገርና በጣም የሚያሳጣኝ አንድ ሰው ነበር። እኔም በሰውዬው ላይ ቂም ይዤ ስለነበር የታጠረውን አጥር አፍርሼ ታጭዶ በተከመረው የሰውዬው እህል ላይ ፍየሎችና መክቶች አስገብቼ አስበላሁበት። ሰውዬው ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ትልቅ እርጩሜ ቀጥፈው ሊይዙኝ ቢሞክሩም እኔ ወደ ሜዳ ሄጄ ቢያሯሩጡኝ ሊይዙኝ የማይችሉበት ቦታ ላይ ቆሜ አያቸው ጀመር፤ በኋላም ተስፋ ቆርጠው ተመለሱ። ከዚህ የተነሳ አንዳንድ የአካባቢያችን ሰዎች ለኔ "ኦኢስ" የሚል ቅጽል ስም አወጡልኝ። "ኦኢስ" ማለት በሃዲይኛ "ተስፋ አስቆራጭ" ማለት ነው።

ይህ ኃይለኛ ባህርዬ እየጨመረ ሄዶ እያደግሁ ስሄድ ጭራሽ ምንም ነገር መፍራት አቆምኩ። በሕይወቴ ፍርኃት የሚባል ነገር ያወቅሁት በ1962 ዓ.ም ነበር። (ይህንን ፍርኃቴን በትክክለኛው ቦታ ላይ አነሳዋለሁ።) ካለ መፍራቴ ባሻገርም ምንም ነገር ሳደርግ አላፍርም ነበር። ለምሳሌ፡- አደግ ካልሁ በኋላ ከልጃገረዶች ጋር እየተላፋሁ ስጫወት እናቶቻቸው መምጣታቸውን ባይ እንኳን አፍሬ ከማቆም ይልቅ እንዳውም የባሰ በእነርሱ ፊት አጓጉል ድርጊቶችን በድፍረት እፈጽም ነበር።

ሌላው በታዳጊነቴ የተጠናወተኝ አንዱ ክፉ ባህርዬ ስርቆት ነበር። ይህን የስርቆት እመሌን ያዳበርኩት ገና በትንሽነቴ የአተር እሸት ከሰው ማሳ በእግሮቼ ላይ እያሰርኩ ከማሳው በማውጣት እና ወደ ማልታይበት ቦታ ወስጄ በመብላት ነበር። ቀስ በቀስም ፍየልና በግ ሁሉ እስከመስረቅ ደረስኩ።

የልጅነት እድሜዬን በእንደዚህ ዓይነት መልካምና ክፉ ባህርያት መካከል ነበር ያሳለፍኩት። በስተመጨረሻም ወደ ጉርምስና እድሜ ስገባ ክፉውና ኃይለኛው ባህርዬ አይሎ ያስቸግረኝ የነበረውን ታላቅ ወንድሜን ገድዬ ሽፍታ ለመሆን አሰብኩ። ታላቅ ወንድሜን የመግደል ምኞት ያሳደረብኝም ሽፍቶች የገዛ ዘመዱን ገድሎ ያልመጣን ሰው ሽፍታ ሆኖ እንዲቀላቀላቸው አይፈቅዱም ሲባል መስማቴ ነበር። ይህን ለማድረግም ከአንድ ሌባ በ42 ጠገራ (የድሮ ማር ትሬዛ ብር) ጠብመንጃ ለመግዛት ተስማምቼ ከጨረስኩ በኋላ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመኔ የሕይወቴ አቅጣጫ ተቀየረ።

# ምዕራፍ ፬

# ከድቅድቅ ጨለማ ...

*ኬዳሞ ገና ታዳጊ ነው። ያኔ ገና የመንገድ፣ የመኪና፣ የባትሪ መብራት፣ አምፖል፣ ማሾ እና ፋኖስ በሃገራችን በደንብ ባልታወቁበት ዘመን መሽቶ ቀኑ ሲጨላልም የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ያከትማል። ሰው ሁሉ በጎጆው ይከተትና ጭል ጭል በምትልና ዓይን በምታጨናብስ የላምባ መብራት ዙሪያ ይሰባሰባል፤ ወይም ምናምን በተጣደበት ምድጃ ዙሪያ ባለ የእሳት ነበልባል ጭላንጭል ብርሃን ፊት ከብቦ ይቀመጣል። በዚህ ወቅት ከቤት ወደ ደጅ የወጣ ሰው እግሩ እንደመራው ይሄዳል እንጂ ምኑን ረግጦ ምኑን ተራምዶ እንዳለፈ አይታወቀውም። በተለይ ደግሞ ወቅቱ ክረምት ወይም ደመናማ ከሆነ የሰማይ ከዋክብትም ሆነ ጨረቃ ብርሃናቸውን ወደ ምድር ማሳለፍ ስለሚሳናቸው ጨለማው ዓይን የሚዋጋ ይሆናል።*

*አንድ ምሽት ላይ ገና ታዳጊ የነበረው ኬዳሞ በምሽት በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ አጎቱ ቤት የግድ መሄድ ነበረበት። መቼም እንደዛሬው የከተማ ልጆች 'ፈራሁ፤ ሰው አብሮኝ ይሂድ' ወይም 'አልሄድም' ማለት አይቻልምና ተነስቶ ጨለማው ውስጥ ገባ። ሰዓቱ ገና ከምሽቱ 2 ሰዓት አካባቢ ቢሆንም ጨለማው ግን ድቅድቅ ብሏል። ኬዳሞም ምንም ነገር ከፊቱ ባይታየውም በቀን ብርሃን በሚያውቀው አቅጣጫ በነሲብ መጓዝ ቀጠለ። በኋላም "ከፊት አንድ ነገር ቢመጣ አይታየኝም፤ ስለዚህ የሆነ አውሬ ከፊቴ ቢኖር ለተት ብዬ አፉ ውስጥ መግባቴ ነው።" ብሎ አሰበና የያዘውን ዱላ ወደሚሄድበት አቅጣጫ ግራና ቀኝ እያወናጨፈ ይጓዝ ጀመር። ምንም ነገር ባይታየውም ከፊት ለፊቱ አንድ ነገር እንዳለ ግን ይሰማዋል። የፈራው አልቀረም የሚወናጨፈው ዱላ አንድ ነገር ነረተ። ትልቅ ጅብ ነበር። ጅቡም ጮኾ ሸሸ። ያ ዱላ ባይወናጨፍ ኖሮ ግን ሊሆን ይችል የነበረውን ነገር ለማሰብ እንኳን ይዘገንናል።*

*የያኔው ታዳጊ ኬዳሞ ይህንን በአስራዎቹ እድሜ እያለ የደረሰ ክስተት እርሱም ሆነ ያደገበት ማኅበረሰብ በክርስቶስ ኢየሱስ ከማመናቸው በፊት የነበራቸውን ሕይወት የሚወክል አድርጎ ያስበዋል። ሕዝቡ ሁሉ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ነበሩ፤ ከፊታቸው ምን እንዳለ እና ወዴት መሄድ እንዳለባቸው ፈጽመው አያውቁም ነበር።*

---

ቀደም ብዬ እንደተረክሁላችሁ የኛ ብሔረሰብ ልዩ ልዩ የባህል ኃይማኖቶችን እየተከተለ በልዩ ልዩ ባለዛሮችና ጠንቋዮች ማስፈራሪያ ተተብትቦ በታላቅ ፍርኃት ውስጥ ይኖር ስለ ነበር ከዚህ ዓይነቱ የጨለማ ሕይወት መውጫም ሆነ አማራጭ ያለ አይመስለንም ነበር። በእርግጥ ከነበረብን የባዕድ አምልኮና በጠንቋዮች በኩል ከሚመጣ የሰይጣን ተጽዕኖ ባሻገር ልዩ ልዩ ኃይማኖታዊ ሥርዓቶችም ነበሩን። በልጅነት አዕምሮዬ ያየሁትን ሳስበውና አሁን በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚደረገውን የአምልኮ ሥርዓት ሳይ በትውልድ ስፍራዬ አካባቢ ክርስትና አስቀድሞ ገብቶ እንደነበረ እገምታለሁ።

ኃይለኛው ወላጅ አባቴ በኛና በመንደሩ ሰው ሁሉ ተፈርተው ይኖሩ የነበረ ቢሆንም እንደማንኛውም ሰው እርሳቸውም የሰይጣን አምልኮ ተሳታፊና ሰይጣንን ለመታዘዝ የሚጥሩ ሰው ነበሩ። አንድ ጊዜ (ከመሞታቸው ትንሽ ቀደም ብሎ) ጣሊያን በወጣበት 1933 ዓ.ም ለሰይጣን የሰባት ቀን ድግስ ደገሱ። በዚህ ድግስ ላይ ለሰባት ቀናት ሰባት ኮርማ ታርዶና ሁሉም ጎሳ የየራሱ ባለዛር ስላለው የየጎሳው ባለዛሮች ተጠርተው መጥተው በዚያ ያድሩ ነበር። ያኔ በሻሾን ሰባት ጎሳዎች ሲኖሩ የሰባቱም ጎሳዎች ባለዛሮች መጥተው ነበር። እነዚህ ባለዛሮችም የየራሳቸው ስም ነበራቸው። ለምሳሌ፡- የሌሞ የአምልኮ መሪ ዛር "ጌራ" ሲባል ትርጉሙ "ሯጭ" ማለት ነው። በአንድ በኩል ከኛ ጋር ይዛመድ ከነበረው ባለዛር ላይ ያደረው ዛር "ጠራቆ" ይባላል። ጠራቆ "የብረት አጥር ሰባሪ" ማለት ነው። ሌላው ደግሞ "ጅንቾ" የሚባል ዛር የነበረ ሲሆን "ጅንቾ" ማለት "አጋንንት" ማለት ነው። በአጠቃላይ ሰባት ባለዛርና ሌሎች ቃልቻዎችም ሁሉ ለድግሱ ተሰባስበው መጥተው እያደሩ ይበሉ እና ይጠጡ ነበር። ከዚያም አባቴ በእናቴ ላይ ደርበው ያገቧት ሴት ነበረችና ባለዛሮቹ ወንድ ልጅ ትወልዳለች እያሉ ተናገሩ። እኛም በጊዜው የትም ሳንሄድ ቁጭ ብለን የሚናገሩትን እንሰማ ነበር። በኋላ ግን የሰይጣን ነገር ውሸት ነውና ትወልዳለች የተባለችው የእናቴ ጣውንት እንኳን ልትወልድ ዓመቱ ሳያልቅ በሐምሌ ወር ሕይወቷ አለፈ።

ምንም በጊዜው ልጅ ብሆንም ከዚህ ለባለዛሮች የተደገሰ ትልቅ ድግስ በፊትም (በዓመት ሁለት ጊዜ ስለሚደገስ) ሌላ ድግስ ተደግሶ እንደነበር አስታውሳለሁ። ጊዜው በጥቅምት ወይም በጥር ወር ይመስለኛል፤ ለአምስት ቀን አምስት ኮርማ ታርዶ፣ የማር ጠጅ፣ የገብስ ቆሎ፣ ቦርዴ እና ሌላም በርካታ መብልና መጠጥ ተዘጋጅቶ ባለዛሮች መጥተው እየበሉና እየጠጡ ያድሩ ነበር። ባለዛሮቹ የተደገሰላቸውን እየበሉ ነገሩ ሁሉ መልካም እንደሚሆን ሲናገሩ ቆይተው ገና እግራቸው ከቤታችን ሳይወጣ አንዲት በጣም የምትወደድ ብዙ ወተት የምትሰጥ ላም ሞተች። አባቴም በጣም ተበሳጭተው ባለዛሮቹን ሊወጉ ጦር ይዘው ተነሱና "ውሸታሞች፣ ውጡ!" እያሉ ሊደበድቡአቸው ሲቃጡ ሴቶች ተሰብስበው አባቴን ለምነው አረጋጉአቸው። አባቴም "ታዲያ ላሚቱ ለምን ሞተች?" ብለው ጠየቁ። ባለዛሮቹም "እይብና ጎመን በአንድ ላይ ተቀቅሎ የሚሰጥ ግብር ነበር። እሱ ስለቀረ ነው" አሉ። አባቴም "እፊር ብሉና ላሟ ሳትሞት ቀድማችሁ አትናገሩም ነበር?" አሉ። በኋላም ላሚቱ ብትሞትም ሌላ ችግር

እንዳይከተል ግብሩ ተሰጠ። ያን ጊዜ ይህን በመሰለ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ነበር የምንኖረው። ከዚህም ሌላ ባለዛሩ አንድ ነገር ቢያምረው ያጓራና ይጠይቃል። እኛም የጠየቀውን ካልፈጸምን ችግር ላይ እንወድቃለን።

እንግዲህ በዚህ አኳኋን እየኖርን እያለ ነው ከላይ የጠቀስኩት የሰባት ቀናት ድግስ የተደገሰው። በዚህ ድግስ ላይ ለእናቴ ጣውንት ከተነገረው በተጨማሪ ለአባቴም ባለዛሮቹ የተለያየ ነገር ተናግረው ነበር። አብዛኛዎቹ "እድሜህ ይረዝማል፣ ብዙ ዘመን ትኖራለህ" ሲሉት አንዱ ባለዛር ግን "እኔ ለአንተ እድሜ አላየሁም ትሞታለህ" አለ። ከዚያም "መፍትሔው ምንድነው?" ብለን ስንጠይቅ "ከደጋ አገር መጋላ፣ ቦቃ ኮርማ ገዝታችሁ አምጡና መስዋዕት አድርጉ" ተባልን። ነገር ግን አባቴ ለነገሩ ብዙም ትኩረት ሳይሰጡ የታዘዙትን ትተው ከከብቶቻቸው መካከል መጋላ ቦቃ ወይፈን መርጠው መስዋዕት አደረጉ። በኋላ በጣም ታመሙና በፊት ችላ ያሉትን መጋላ ቦቃ ኮርማ ከደጋ አገር ገዝተው አምጥተው አረዱ። ቢሆንም ሳይሻላቸው ቀርቶ ጥቅምት 1 ቀን 1939 ዓ.ም አረፉ። ይህም በፊትም ጥያቄ ይሆንብኝ የነበረውን የሰይጣን አሠራር ይበልጥ እንድመረምር አደረገኝ።

ያኔ የነበርንበት የኑሮ ሁኔታ ከአስከፊው የሰይጣን አገዛዝ የተነሳ መሄጃ ያጣንበት ነበር። ሰይጣን ሁልጊዜ በሞት ያስፈራራን ነበር። ባለዛሮች ሁልጊዜ ወደኛ ይመጡና «ይኸን አምጡ፤ ካላመጣችሁ ትሞታላችሁ» ይሉናል። በእግዚአብሔር ቃል ላይ *"እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።"* ይላል (ዕብ. 2፡14-15)። ነገር ግን እኛ ማምለጫ የምንለው ነገር ፈጽሞ አልነበረንም። ከዚህ አልፈን የመኖርን ትርጉምና ሰው ማለት እራሱ ምን ማለት እንደሆነ አናውቅም። ለኛ መኖር ማለት መብላት፣ መጠጣት፣ መልበስ፣ መሞት፣ መጥፋት ብቻ እንጂ ወደ ፊት ይህ ተስፋ አለን የምንለው ነገርም ፈጽሞ አልነበረንም። በአጠቃላይ ሊገለጽ የማይችል ድቅድቅ ጨለማ ውጦን እንኖር ነበር።

የነበርንበትን ጨለማ አስከፊነት የተረዳነው ግን እግዚአብሔር በወንጌሉ ብርሃንን ሲያበራልን ነበር። እግዚአብሔር ሁልጊዜ በመጀመሪያ የሚሠራው ሥራ ብርሃን ማብራት ነው። የነበርንበት ጨለማም እንዴት ድቅድቅና ብርሃን የሚያስፈልገው እንደነበር የሚያሳየው ከላይ የተተረከው የ15 ዓመት ልጅ እያለሁ ከፊት ጆብ ለፊቴ ቆሞ ምንም ማየት ያልቻልኩበት አጋጣሚ ሲሆን ሌላው በሁለት አንቶቼ ላይ የደረሰው አጋጣሚ ነበር።

እነዚህ የእናቴ ወንድሞች አንድ ምሽት ላይ በበረት ያሉ ከብቶችን ሲጠብቁ ቆዩና አንደኛው እራት ሊበላ ወደ ቤት ሲሄድ ሌላው ከብቶቹን ሊጠብቅ በረት ውስጥ ቆየ። ሆኖም የተወሰነ ሰዓት ቆይቶ ሌላ የሚጠብቅለት ሰው ስላገኘ ሁለተኛውም በረቱን ትቶ ወደ ቤት መሄድ ጀመረ። በዚህ ጊዜ በመጀመሪያ የሄደው እራቱን በልቶ ያኛውን

ሊቀይር እየተጣደፈ ሲመለስ በመንገድ ሁለቱ ይገናኛሉ። በጊዜው ጨለማው በጣም ድቅድቅ ስለነበር ሁለቱም ከፊት የሚተናኮላቸውን ለመውጋት ጦራቸውን ወድረው ይጓዙ ስለነበር ወንድማማቾቹ እርስ በእርስ ሲገናኙ ሊወጋጉ ብለው እርስ በእርስ በጦር ከተሚጫጩ በኋላ በድምፅ በመተዋወቃቸው ለጥቂት ተረፉ። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ያኔ የነበርንበትን የጨለማ ሕይወት የሚያሳዩ ጥሩ ማስረጃዎች ናቸው።

## የእግዚአብሔር ብርሃን

ጌታን ያመንኩትና እውነተኛው ብርሃን የበራልኝ ዘግየት ብሎ ቢሆንም የእግዚአብሔር መኖር ግን እንደ ጭላንጭል ብርሃን በሕይወቴ ከሕጻንነቴ ጀምሮ ብልጭ ይል ነበር። የመጀመሪያው ገና በስምንት ዓመቴ ሰይጣን ለአባቴና ለቤተሰቦቼ በባለዛሮች አማካኝነት የሚናገረው ሁሉ ውሸት በሆነ ጊዜ በሰይጣን ላይ የነበረኝ እምነት በመጥፋቱ የተፈጠረ ነው። ከዚህ የተነሳም "ሰይጣን ውሸታም በመሆኑ ምንም አይሠራም" እል ነበር። ሌላው ደግሞ በዚያው እድሜ እያለሁ የፍየሎችና የጥጆች እረኛ ሆኜ ወደ ሜዳ በምወጣበት ጊዜ ሜዳ ላይ እያለሁ ዝናብ ሲመጣ የምጠለልበት ምንም ዓይነት መጠለያ አልነበረኝም። ስለዚህ እጄን ዘርግቼ "እኔን የፈጠርከኝ አምላክ ሆይ ይህ ዝናብ እንዲመለስ አድርግ" ብዬ ፊቴን ወደ ዝናቡ አዙሬ እለምናለሁ፤ ወዲያው ዝናቡ ይቆማል፤ እኔም "ጎሽ! እግዚአብሔር አለ" እላለሁ።

ሰዎች የሞተ ሰው ለቀብር ሲወስዱ ስመለከትም "ሰው ከየት መጣ? ወዴት ይሄዳል?" በማለት የራሴን እጆች ዘርግቼ እያየሁም "እነዚህስ ወደፊት ምን ይሆናሉ? እኔስ ከየት ነው የመጣሁት? ወዴትስ እሄዳለሁ? ምንስ እሆናለሁ?" እያልኩኝ ጥልቀት አስባለሁ።

በዚህ ዓይነት ጥያቄዎች በተሞላ ሕይወት ውስጥ እያለሁም አባቴ ሞቱ። አባቴ በተቀበሩ በአምስተኛው ቀን ዘመዶቼ አንድ ሥርዓት ያስፈጽሙ ጀመር። በባህላችን መሠረት ሰዎች ከቀብሩ በኋላ አንድ ከብት ይሰዉና ሁለተኛ ሞት እንዳይደገም ለማድረግ ደግሞ አንድ በግ ወስደው ሜዳ ላይ ያርዳሉ። በጉን በሚያርዱበት ወቅትም ስለ አባቴ "በግራ በኩል ካለ ወደ ቀኝ መልሰው" ይላሉ። እኔም ያኔ ይህን በትኩረት እሰማ ስለነበር "ለካስ በሰማይ ሌላ አገር አለ" አልኩኝ። እንደገና ለአባቴ መታሰቢያ ደግሞ በሰባተኛውም ቀን ሌላ ላም ይዘው በማለዳ ሄዱ። ይህም ተዝካር ሳይሆን በኛ ባህል "ኢዶታ" የሚባል ስርዓት ነው። በመቃብር ቦታው ላሚቷን አርደው ሽማግሌዎች ሲነጋገሩ እኔ ምንም እንኳን የ11 ዓመት ልጅ ብሆንም ሁሉንም ልቅም አድርጌ ሰምቼ እመረምር ነበር።

ከላይ እንደገለጽኩት የባለዛሮቹና የሰይጣን ነገር በጣም ጥያቄ የሚፈጥርብኝ ወደ እግዚአብሔር እንዳይ ምክንያት መሆኑ ነው። በባለዛሩ ላይ ጥያቄ መፈጠሩና መጠራጠሬ ደግሞ ከልጅነቴ ጀምሮ አብሮኝ የቆየ ነገር ነው። አንድ ጊዜ እንደውም አባቴ ከመሞታቸው በፊት እኛም ቤት አንዱ ታላቅ ወንድማችን ባለዛር ስለነበር አባቴን "ሜቻቶ ... ሜቻቶ" ብሎ ደጋግሞ ተጣራና "ካንተ በስተቀር ልጆችህ ለኔ

አይሰግዱም፤ .. ወደ ፊት እኔን እርባ ክንድ እርቀው ይቀበሩኛል፤ ስለዚህ ስንቅ ስጠኝ ከዚህ ልሄድ" አለው። አባቴም "ወዴት ልትሄድ ነው?" ሲለው "እኔ ከጊቤ ወንዝ ማዶ እሄዳለሁ። ወደ ጅማ እሸሻለሁ" ብሎ መለሰ። ይህ ሲሆን እንግዲህ ወንጌል ገና ወደኛ አካባቢ አልመጣም ነበር። እኔና ሌሎች ወንድሞቼ ቁጭ ብለን የሚናገረውን እንሰማ ነበርና እኔ "ምን ሊሆን ነው?" ብዬ ራሴን እጠይቅ ነበር። ሁልጊዜ ዛሩ ወንድሜን ሲያስጓራው እኔ መተኛቴን ትቼ መንፈሱ የሚያደርገውን እከታተል ነበር። በዚህ ጥያቄ ውስጥ እያለሁም አባቴ ሞቱና ተወልደን ያደግንበትን የአባታችንን መሬት ትተን ወደ ሌሞ ቃልሻ ሄድን።

እኛ ከአባታችን የወረስናቸውን ከብቶች ይዘን ቃልሻ ስንደርስ በአካባቢው እና በአባቴ ዘሮች መካከል ወንጌል ተሰብኮ ሰዎችም አምነዋል። ያኔ እኔ አባቴ በ11 ዓመቴ ሞተው አንድ ዓመት ቆይተን 12 ዓመት ሲሆነኝ ነበር የሄድነው። በዘመኑ ያሙኑ ሰዎች "ሐንክ መና" ወይም "የሱስ መና" ነበር የሚባሉት። "ሐንክ መና" ማለት "የእውነት ሰዎች" ማለት ነው።

እኔም ገና ይህን ነገር ሳይ "ለካ ያ ዛር ሲናገር የነበረው ይህንን ነው" አልኩኝ። ዛሩ ለአባቴ "ልጆችህ እኔን አያመልኩም፤ ለኔ አይገብሩም።" ያለው ይህንን ኖሯል። ትንሽ ቆይቶም ልቤ ከእምነቱ ጋር ፈጽሞ ተቀራኝ። ነገር ግን እኛ የምንኖረው ሻሾጎ ስለሆነ ካመንን በኋላ እንዴት መኖር እንችላለን በማለትና እኔ የታሰርኩባቸውን ልዩ ልዩ ኃጢአቶች መተው ከባድ መስሎ ስለታየኝ ለመወሰን ተቸገርኩ። ይሁንና በዚህ ጊዜም የተለመደውን ከዘር የወረስነውን ለሰይጣን የሚደረግ ሥርዓት አልተውንም ነበር። ስለዚህም አባታችን ከሞቱ በኋላም በዓመት ሁለት ጊዜ ለሰይጣን ድግስ እናዘጋጅ ነበር። ክርስቶስን እምነን እስከወሰንበት ጊዜ ድረስ ከድግሱ አልፈን ባለዛሩ በፈለገው ጊዜ ሁሉ ሲያጓራ ሄደን እንጠይቅና ያዘዘንን እንደቃሉ እንፈጽም ነበር። አባታችን ከሞቱ በኋላ ባለዛሩ የገዛ ወንድማችን ስለሆነ ችግሩ የባሰ ሆነ።

ባለዛሩ ወንድሜ አባታችን ከመሞታቸው በፊት በውርስ የሚደርሰውን ከብት ወስዶ ተለይቷል። ቢሆንም በጊዜው (ከ5 ዓመት በፊት) 27 ያህል ላሞች ወስዶ በደንብ ስላልጠበቃቸው አልቀውበት 5 ላሞች ብቻ ቀርተውታል። በእናታችንና በኛ እጅ ያሉት ላሞች ደግሞ 90 ደርሰው ነበር። በዚህ ጊዜ ባለዛሩ ወንድሜ ከኛ ላሞች ላይ እንዲሰጠው ለቤተዘመድ ከሰሰን። እናቴና ከኛ ጋር ያለው ታላቅ ወንድሜም «ከዚህ ቀደም አባታችንን ለዘመዶቻችን ከሰህ 27 ላሞች ወስደሃልና አንሰጥህም» አሉት። በዚህ ወቅት እኔ በልቤ «እኛ ልጆች ነን እርሱ ግን የልጆች አባት ነው። እኛ ይህን ሁሉ ከብት ይዘን ብንኖር ምን ይጠቅመናል?» እያልኩ ነበር። በኋላም የጎሳ ዳኞች የሆኑት ዘመዶቻችን እስቲ ትንሹ ልጅም ይጠየቅ ብለው የእናቴ ልጅ የሆነ አንድ ወንድሜ መጥቶ እኔን ጠየቀኝ። «ምን እንበል? 'እርሱም መልስ መስጠት አለበት' ብለውሃል» አለኝ። እኔም «እኔና አንተ ገና እድሜያችን ትንሽ ነው። ከብቶችም ከኛ ጋር እያደጉ ይበዛሉ። እርሱ ግን እድሜው ትልቅ ነው። የልጆች አባትም ነው። እርሱ

ደኃ ሆኖ እኛ ብንበለጽግ ምን ይጠቅመናል? እናካፍለው፡፡›› ብዬ አሳመንኩት፡፡ ይህን ሀሳባችንን እናታችን ማታ ሲጠይቁን ነገርናቸውና ተቆጡን፡፡ ነገር ግን ‹‹እርሱ የእናቱን ድርሻ 27 ላሞች ከስሶ ወስዷል እንደገና እንዴት ይካፈላል?›› ሲሉን እኔ ‹‹አይ እኛ ልጆች ነን ከብቶቹ ከእኛ ጋር ማደጋቸው አይቀርም፤ እርሱ ታላቃችንና የልጆች አባት ሆኖ ደኻ ከሚሆን እኛ ብናካፍለው ይሻላል›› ስላቸው በጊዜው ምንም ልጅ ብሆን እናቴ ሰምተውኝ ሃሳቤን ተቀበሉና ‹‹ካላችሁ እሺ›› ብለው ላሞቹን ተካፈልን፡፡ ወንድሜም በተለያዩ ምክንያቶች 35 ላሞች ደርሰውት ወሰደ፡፡

# ምዕራፍ ፫

# ብርሃኑ ሲበራ

ኬዳም በመጠጥ፣ ሴቶችን በመወዳጀት፣ በዘፈን እና በሌሎች የወጣትነት አጓጊ ዓለማዊ ነገሮች ፍቅር በመያዝ ራሱን ሞልቶ ሲኖር ሳለ እግዚአብሔር የወንጌሉን መልእክት አስሸክሞ ከከምባታ ምድር የላካቸው ወንጌላውያን የኬዳሞን መኖሪያ መንደር ሻሾጎን በወንጌል ዘመቻ መውረር ጀመሩ። ከኬዳም ወገኖችም አንዳንዶች አመኑ። ያመኑት ወገኖችም ፈጥነው ኬዳሞን እና ሌሎች በባእድ አምልኮ ተተብትበው የሚሰቃዩ ወገኖቻቸውን ለማዳን የምስራቹን ለመንገር ይጥሩ ጀመር።

አንድ እሁድ ወጣቱ ኬዳም ገለቶ ኮኬቦ ከሚባል በቅርቡ በወንጌል ያመነ ዘመዱ ጋር ተቀምጦ ይጨዋወታል። ቦታው የሻሾጎን ምድር ከሞሉት ሜዳዎች በአንዱ ዳርቻ ነበር። ኬዳም በዚህ ሜዳማ ምድር ገና ከልጅነቱ አንስቶ ከብቶች እያገደ ከእኩዮቹ ጋር እየተሯሯጠ ቦርቆበታል። በዚህ ምንም መጠለያ በሌለው ገላጣ ሜዳ ላይ ከብቶች ሊያሰማራ በክረምት ዝናብ የተቀጠቀጠበት ጊዜም ብዙ ነበር። ወቅቱ በጋ ሆኖ ሐሩሩ ሊበረታ አልፎ አልፎ በተተከሉ ዛፎች ሥር ተሸሽጎ በሜዳው ነፋሻማ አየር ራሱን ዘና አድርጓል። በማለዳ ከብቶቹን ይዞ ወጥቶም በውርጭማው ወራት ጉንጮቹን እና የእጆቹን አይበሉባ ቀጭ አበላሽቶአቸዋል።

ከሁሉም ወቅቶች ግን ኬዳም በተለይ የክረምት ዝናብ አይሎ በግራም ሆነ በቀኝ ቢሄድ የሚጠለልበት አጥቶ ዝናቡ ሰውነቱን አረስርሶት አንጀቱ በብርድ የተንሰፈሰፈበትን ጊዜ አይረሳውም። በዚህ ብርድ ሰውነቱን በሚያንቀጠቅጥበት ሁኔታ ውስጥ ጥርሶቹ እየተንገጫገጩ በተኮላተፈ አንደበት "የፈጠርከኝ አምላክ የእውነት አንተ ካለህ ይህንን ዝናብ አቁምልኝ፣" ብሎ ዝናቡን የማያውቀው አምላክ ሲያቆምለት በተደጋጋሚ አይቷል።

በዚህ ለንበትም ኬዳም ከልጅነት የዕድሜ ክልል ወጥቶ ጠንካራ ወጣት ስለ ከዘመዱ ገለቶ ጋር ተቀምጦ የሚጨዋወተው ስለ እግዚአብሔር ነበር። በዚህ የሻሾጎ ሜዳማ ስፍራ ላይ በክረምት ብቻ የሚፈሱ ወንዞች ቦርቡረው የሠሩት ሸለቆ እና ትላልቅ የተፈጥሮ ቦይ ተጠላልፎ ተሰማምሯል። ኬዳም እና ገለቶ ከጸሐዩ ሙቀት ለመከለል ዛፍ ሥር ተቀምጠው ያወራሉ። በሜዳው ላይ አጋጅ አጥቶ እንደፈለገ የሚነፍሰው ነፋስም የሁለቱን ወጣቶች ሰውነት ከሙቀቱ ቀዝቀዝ ያደርግላቸዋል።

*በዚህ ውይይት ላይ ገለቶ ደጋግሞ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያነሳ ነበር። ኬዳሞም ገና በታዳጊነቱ አውላላ ሜዳ ላይ ከብቶች አሰማርቶ እያለ የሚመጣውን ዝናብ ልመናውን ሰምቶ ሲያቆምለት በማየት ስለመኖሩ እርግጠኛ የሆነው ፈጣሪ ይህንን መጽሐፍ እንዴት እና መቼ ለሰው ልጆች እንደሰጠ ይጠይቅ ጀመር። ገለቶም አዲስ አማኝ ነውና መጽሐፍ ቅዱስን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ መቼ፣ እንዴት እና በማን እጅ እንደሰጠ ያወቃትን ያህል ለኬዳሞ ለማስረዳት ሞከረ። ልክ ሜዳው ላይ የሚነፍሰው ነፋስ ሰውነታቸውን ቀዝቀዝ እያደረገ ይፈጥርባቸው እንደነበረው የደስታ ስሜት ገለቶ ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ቃሉ የሚናገራቸው ቃላት የኬዳሞን ልብ ቀስ እያሉ በደስታ ስሜት እና ስለ እግዚአብሔር ተጨማሪ ለመስማት በመጓጓት መሻት ያነሳሱት ጀመር።*

-------------------------//-------------------------

እኔና ገለቶ ሜዳው ላይ ቆም ብለን ስንጨዋወት ከቆየን በኂላ እኔ ይህንን እምነት ለመቀበል መጽሐፍ ቅዱስን እግዚአብሔር ለማን፣ መቼ እና እንዴት እንደሰጠ ማወቅ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ። ገለቶም ጥያቄዬን ለመመለስ የቻለውን ያህል እየነገረኝ እኔም በምሰማው ነገር ውስጤ ደስ እየተሰኘ ከተቀመጥንበት ተነሳን።

እኔ ወደ አንድ ለቅሶ ቤት መሄድ ስለፈለግሁ ገለቶም አብሮኝ ሊሄድ ተስማምቶ ከተቀመጥንበት ተነስተንም ጉዞ ጀመርን። ውይይታችንንም በመንገድ ላይ በመቀጠል ለአርባ ደቂቃ ያህል እያወራን ተጓዝን። እኔም ከእርሱ በምሰማው የወንጌል ቃል ልቤ ደስ እየተሰኘ ብዙ መስማት እየፈለግሁ ነበር።

መንገድ ላይ እየተወያየን እየሄድን እያለም የሚች አባቴ ዘመዶች አገኙንና አማኝ ከሆነው ገለቶ ጋር ስለ እምነት እያወራሁ እንደሆነ ሲያውቁ በጣም ቅር ተሰኙ። እየተቀባበሉም ‹‹አንተ አድገህ ትልቅ ሰው ሆነህ፣ በሀብት እና በሥልጣን አድገህ ከአባትህ በላይ እኛን የምታስጠራ ትሆናለህ ብለን ስንጠብቅ ጭራሽ ከእነዚህ እርኩሶች ጋር ትገጥማለህ?›› ብለው አፈጠጡብኝ።

እኔም በጊዜው በሰማሁት ነገር ደስ እየተሰኘሁ የነበረ ቢሆንም የአባቴ ዘመዶች እኔን ከፍ ከፍ በማድረግ እያሞገሱ ማመኔን ሲቃወሙ ምንም ልናገራቸው አልደፈርኩም። በዚሁ ሁኔታም ምንም ምላሽ ሳልሰጥ ሁላችንም ለቅሶው ቤት ገብተን ተቀመጥን። ከቆይታ በኂላም ወደየመጣንበት ተበታተንን።

ይህ አጋጣሚ በተፈጠረ ልክ በሁለተኛው ሳምንት ሰንበት ታላቅ እህቴ ለሰይጣን የሚሆን ግብር ከቤቷ ወደ እኛ አመጣች። ያንን ግብር ሊታደሙ እና ሊበሉ ባለዛር የሆነው ታላቅ ወንድሜን ጨምሮ አምስት ባለዛሮች መጡ እና እየመረቁ ግብሩን ይበሉ ጀመር። ይኸው ግብር እየተበላ እያለም ባለዛሮቹ መልሰው እኔና የቅርብ ታላቅ ወንድሜ የሆነው ፈይሳን "ትሞታላችሁ" ብለው ተናገሩ። ልክ ይህ ሲነገር ሌሎቹ ሲደነግጡ፣ እኔ ግን በጣም ተቆጣሁ። ምክንያቱም ልክ ከ15 ቀን በፊት ገለቶ ለኔ ወንጌልን በነገረበት እለት ማታ "ለሚቻቶ ልጆች ብርሃን ይወጣል፣ ታላቅም ትሆናላችሁ።" ተብለን ነጭ ኮርማ ለባለዛር ገብረን ነበር። በ15ኛ ቀኑ እንዲህ ስንባል

"ብርሃን የሚወጣልን ለአስራ አምስት ቀን ብቻ ነው እንዴ?" አልኩ እና በጣም ቅር አለኝ።

እዚያው በተቀመጥኩበትም "በቃ ቢገድልም ይግደለኝ ክርስቶስን አምናለሁ፤ አምኜ ብሞት ነፍሴ ትድናለች" ብዬ ወሰንኩ። እናቴ ግን ተነስተው እኛ ከሞት እንድንድን መደረግ ያለበትን ለማወቅ ቃልቻዎቹን ይለማመኑ ጀመር።

ባለዛሮቹም እኔ ጥቁር በቃ ታላቅ ወንድሜ ደግሞ ቀይ በቃ ኮርማዎች እንድንሰጥ ሲወስኑ በስፍራው የነበሩ ሰዎችም ፈርተው እሺ እሺ ብለው እጅ ነሱ፤ እኛም ተነስተን የተባለውን ለመፈጸም እጅ እንድንነሳ "ተነስ፣ ተነስ" ሲሉኝ "የዛሬ 15 ቀን 'ለሚቻቸ ልጆች ብርሃን ይወጣላችኋል' ተብለን ነጭ ወይፈን ሰጠን። ብርሃን የሚወጣልን ለ15 ቀን ብቻ ነው? እኔ በዚህ አልስማማም፤ ስለዚህ አልነሳም።" አልኩ። ይህን ሲናገር የነበረው ባለዛርም ዝም አለ።

እኔም በውሳኔዬ መሠረት በማግስቱ ሰኞ ጌታን ልቀበል ከቤቴ ወጣሁ። የሚገርመው ግን በጊዜው ጌታን እንድቀበል ሲነግሩኝ እኔም ሳላግጥባቸው፣ ስሰድባቸው እና ስጣላቸው የነበሩ አማኞች እኔ በፈለግኳቸው ቀን ሊገኙ አልቻሉም። በጠዋት ወጥቼ ስፈልጋቸው ቆይቼ አንድም አማኝ ስላላገኘሁ ተመልሼ ወደ ቤት ገብቼ ምሳ እየበላሁ እያለም ውጪ ደጃፍ ላይ ስትጫወት የነበረች ታናሽ እህቴ ክርስቶስን ለማመን ፈልጌ አማኞቹን እየፈለግሁ እንደነበር ስላወቀች ጠራችኝና "የምትፈልጋቸው ሰዎች እነዚህ አይደሉም?" አለችኝ። ለካስ ሃይሌ በሚባል ቦታ መጽሐፍ ቅዱስ ሊማሩ የሚሄዱ ሰዎች በኛ ደጃፍ አልፈው ወደዚያ እየሄዱ ነበር። እኔ ምሳዬን ትቼ እነርሱን ተከታትዬ ሄጄ የሚማሩበት ቤት ስገባ ቢያዩኝም ዝም ብለውኝ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናታቸውን ቀጠሉ።

ወኋላም ከዚህ ቀደም ወንጌል ሲነግሩኝ እደበድባቸው እና እሰድባቸው ስለነበር እኔ ሄጄ ቁጭ ስል ማንም ሰው ደፍሮ ሊያናግረኝ አልሞከረም።

እኔም ዝም ብዬ ቁጭ ብዬ ቆየሁ። እነርሱም ፈርተውኝ ዝም አሉ። በዚህ ጊዜ ሰይጣን አንድ ሃሳብ አቀበለኝ። ‹‹እኔ ለማመን ብፈልግም እነርሱ ይኸው ምንም አላሉኝም፤ ስለዚህ ስለኔ ሕይወት እነርሱ ተጠያቂ ናቸው። በቃ እኔ አልጠየቅም።" ብዬ ልወጣ ተነሳሁ። ጌታ ግን እንዴ ሊያድነኝ ወዲል እና መኖሮ የሚባል ዛሬ ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ለመሆን የበቃና ያኔ የሰባት ዓመት ሕፃን ልጅ የነበረ "ጋሽ ኬዳሞ አንተ ግን ለምን ክርስቶስን አታምንም?" አለኝ። እኔም ሁሉም እየሰሙ "ይኸው ክርስቶስን ልመን ብዬ ብመጣ እነርሱ እመን አላሉኝም፤ በእግዚአብሔር ፊት ስለእኔ ነፍስ የሚጠየቁ እነርሱ ናቸው።" አልኩት። እነርሱም "እኛ ዝም ስላልንህ አውቀህ ነገር ፈልገህ ነው እንዲህ ያልከው" አሉኝ።

"እኔ ነገር ፈልጌ አይደለም የመጣሁት፤ ክርስቶስን ማመን ፈልጌ ነው"

"እስኪ ሰይጣንን ክጃለሁ በል" ሲሉኝ

ጌታን ለመቀበል ያስመጣኝ ቀድሞውንም የሠይጣን ማስፈራራት ስለነበር "ሠይጣን 40 ክንድ ወደታች ይቀበር" ብዬ ስጮህ ሁሉም ደነገጡ። ከዚያ ወዲያው ስለ ወንጌል ነግረው ጌታን እንዳምን አስረዱኝ። ወንጌልንም አመንኩ። ከዚያም ወዲያውኑ ወደ ቤቴ መመለሴን ትቼም እዚያው ቁጭ ብዬ ያው እመን ያለኝ የሰባት ዓመቱ ሕፃን መኖሮ እያስተማረኝ ፊደል ስቆጥር ማንበብ ስለማመድ ዋልኩ። ባገኘሁት አዲስ ሕይወት ተደስቼ የክርስትና ሕይወት ልለማመድ አስራ አንድ ሰዓት ተኩል ድረስ እዚያው ቆይቼ ወደ ቤቴ ልሄድ ተነሳሁ።

ወደ ቤት ተመልሼ ወደ ሰፈራችን ስደርስም እናቴ እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው ትልቅ አጣና ይዘው ደጅ ቆመው ጠበቁኝ። ለካስ ወሬኞች በዚያው ባመንኩበት ቅጽበት ወደ ቤት ሄደው የእኔን በክርስቶስ ማመን አይተው "ልጅሽ ተበላሸ" ብለው ነግረዋቸው ኖሯል። እናቴ ከቤታችን ደጃፍ ራቅ ብለው ቆመውም እኔ አገር ሰላም ብዬ በክርስቶስ በማመኔ የተሰማኝን ደስታ እያጣጣምኩ ወደ ቤት ስቃረብ፤ በያዙት የብረት መዝጊያ አጣና እያስፈራሩ "ውቃቢዬን ክደህ የዘሬን አምላክ ትተህ እዚህች ቤት አትገባም!" አሉኝ።

በክርስቶስ በማመን ስለ ክርስቶስ የመነቀፍ ፈተና ገና ባመንኩበት የመጀመሪያው እለት አጋጠመኝ። እኔም እናቴን ለማሳመን ጥረት ማድረግ ጀመርኩ።

"እርስዎን እኮ እኔ ከድሮው ይልቅ እወዶታለሁ፤ አከብሮታለሁ።" ስላቸው "የኔን ውቃቢ ጃራና ኢዶታን ክደህ እኔን ማክበርህን አልፈልገውም።" አሉኝ። እኔም እሺ ብዬ በአዕምሮዬ "የት ሄጄ ልደር?" ብዬ እያሰላሰልኩ ወደ መጣሁበት መመለስ ጀመርኩ። በቀስታ እየተጓዝኩ እያለም እናቴ "ና ተመለስ።" አሉኝ። እኔም "ኢየሱስን ይገፍ ወይስ ..." ስል

ትንሽ አቅማሙና "ይዘህ ና" አሉኝ።

እኔም የመጀመሪያውን ፈተናዬን በድል ተወጥቼ ደስ እያለኝ ወደ ቤቴ ገባሁ።

እኔ ጌታን ባመንኩ በማግስቱ ሰዎች በክርስቶስ እያመኑ ነጻ በመውጣታቸው ግብር የቀረባቸው ባለዛሮች ተበሳጭተው ማክሰኞ ዕለት ከጎሳ መሪዎች እና የአገር ሽማግሌዎች ጋር ተነጋግረው የወንጌሉን መስፋፋት ሊያስቆሙ ተነሱ። ሽማግሌዎቹ ጉዳዩን ለአካባቢያችን ባላባት ለግራዝማች ዳድቼ ሄደው ነገሩ።

በጊዜው የኛ አካባቢ ሰዎች የሆኑ ብዙ ሰዎች ወንጌልን እያመኑ ከሰይጣን ባርነት ስላመለጡ ሁኔታው ትልቅ ስጋት ሆኖባቸው ነበር። ከኛ ቤተሰብ ብቻ እኔን ጨምሮ ሰባት ሰዎች አመንን። ከባለዛሮቹ አንዱ የሆነው የኔ ታላቅ ወንድምም እኔ ሳምን በመበሳጨቱ ነበር ሌሎቹን ሁሉ ያነሳሳው። ግራአዝማች ዳድቼም በወቅቱ የወረዳችን ገዢ ለነበሩት ለፊታውራሪ ከበደ ጉዳዩን ነግረው የተጀመረውን የወንጌል መስፋፋት ግስጋሴ ሊያስቆሙ ተነሱ።

ወረዳ ገብተው ተመድበላቸውም አራት ፖሊሶችን ይዘው በመምጣት በአካባቢው ያሙትን ሁሉ ሰብስበው መደብደብ እና ማሳደድ ጀመሩና እኔንም ይዘው ሊደበድቡ ይፈልጉኝ ጀመር። ረቡዕ ዕለት ማታም አቶ ሹሞሮ የሚባል የኔ የአጎት ልጅ ሁኔታውን አይቶ ሊመክረኝ ፈልጎ እኔ ከብቶች ወደ በረት እያስገባሁ እያለ ወዳለሁበት መጥቶ፡- "ኬዳሞ ይህቺ ሳምንት እስክታልፍ ብቻ ይህን እምነት ተው።" አለኝ። እኔም ባልተው ምን እሆናለሁ?" አልኩት

ትያዛለህ" አለ።

ከዚያስ?" አልኩት፤

ትታሰራለህ"

ከዚያስ?"

ትደበደባለህ"

ከዚያስ?"

ትገረፋለህ"

ከዚያስ?"

ያንተ ከብቶች ከሌላ ከብት ጋር ተቀላቅለው መሠማራት አይፈቀድላቸውም...፣ ቀትሞቱ የሚቀብራችሁ አታገኙም..." እያለ ብዙ ነገር ዘረዘረ። እኔ አሁንም "ከዚያስ?" ማለ የሚናገረው ሲያልቅበት ተበሳጭቶ "ምን ከዚያስ ከዚያስ ትላለህ?" ብሎ በኃይል ጮኸብኝ። እኔም "ስማ እኔኮ ክርስቶስን ያመንኩት ስሞት በእርሱ በማመኔ ነፍሴ ድና ወደ እግዚአብሔር ለመሄድ ነው፤ ስለዚህ እናንተ ደስ ካላችሁ እኔን አርዳችሁ ስጋዬን ተከፋፍላችሁ ብሉ።" አልኩትና በጣም ደነገጠ። በጊዜው ከእኔ ሌላ የእርሱ ታናሽ ወንድምም ክርስቶስን አምኖ ስለ ነበር "በቃ ሁለቱንም ወንድሞቼን አጣሁ" ብሎ ያለቅስና ይለማመጠኝ ጀመር። በመጨረሻም ተስፋ ቆርጦ ትቶኝ ሄደ።

ሐሙስ ዕለት ከብቶች በረት አስገብቼ ከዘጋሁባቸው በኋላ ወደ ቤቴ ሄድኩ፤ እንዳይዙኝም በአቅራቢያው የተሠራች ትንሽ ጎጆ ቤት ውስጥ አልጋ ስለ ነበረ እዚያ ገብቼ ምሽቱን ለማሳለፍ ወሰንኩ።

እዚያች ጎጆ ውስጥ አልጋ ላይ ተቀምጬም በነበረው ሁኔታ ተጨንቄ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አስብ ጀመር። በጊዜው ጌታን ከተቀበልኩ ገና ሦስተኛ ቀኔ ነበረ። ማንም እገሊጋይ ወደ እኔ መጥቶ እንዴት መጸለይ እንዳለብኝ ስላላስተማረኝ ጸሎት አላውቅም ነበር። ነገር ግን ጌታን ወደ ሕይወቴ ስጋብዝ ወደኔ የመጣው የእግዚአብሔር መንፈስ አብሮኝ ስለነበር ባጋጠመኝ ስደት ዙሪያ በአልጋዬ ላይ ተቀምጬ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እያሰብኩ "ምን ልሁን?" እያልኩ ሳለሁ "ጸልይ" አለኝ።

ከተቀመጥኩበት አልጋ ወርጄ ተንበርክኬ ጸሎት ጀመርኩ። "እኔን የፈጠርከኝ አምላክ አመሰግንሃለሁ። አሁን ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አሳየኝ።" ብዬ ጸሎቴን ጨርሼ ወደ አልጋዬ ተመልሼ ተቀመጥኩ። በተቀመጥኩበት ሆኜ እንደገና "ምን ልሁን?" ስል "ሽሽ" የሚል ጉልህ ድምጽ ሰማሁ።

በዚህ መልኩ አድሬ ልክ ከለሊቱ አስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ልሸሽ ተነሳሁና ወንድሜ አንድ ፖሊስ ይዞ እኔን ሊይዙ ወዳለሁበት ሲመጡ በቤቱ ቀዳዳ አየኂቸው።

እኔም ፈጥኜ በጓሮ ውሃ በበረበረው ወንዝ ይሄድበት በነበረ ሸለቆ በኩል አድርጌ አመለጥኩኝ። ተከታትለው ሊይዙኝ መጡ እና እኔ ከሸለቆው ከወጣሁ በኂላ ተከትለው ወደ ሸለቆው ሲገቡ ሲሉም በድንጋይ ለመምታት አስፈራራኂቸው። በዚህ ጊዜ ፖሊሱ የያዘውን ጠመንጃ ወደኔ ሊያነጣጥር ሲሞክር "ተኩሰህ አንድ ነገር ብታደርገኝ ወንድሜ በያዘው ጦር ከመሬት ያጣብቅሃል።" አልኩት። ምንም ማድረግ ስላልቻሉም ባሉበት ዝም ብለው ቆሙ። እኔም በሩጫ ጫካ ውስጥ ገብቼ አመለጥኳቸው።

ከዚያች ሐሙስ ማለዳ ጀምሮም ከእኔ አንድ ቀን ቀድሞ ካመነው ሊረሞ የሚባል ዘመዴ ጋር ለአንድ ሳምንት ያህል ቀን ቀን በጫካ ውስጥ ተደብቀን አሳለፍን። እሁድ ሲመጣም በኛ አካባቢ ወደ ነበረው ጸሎት ቤት እንዳንሄድ ባላባቱ ከአገር ሽማግሌዎች እና ከባላዛሮች ጋር ሆነው ፖሊሶቹን ይዘው ጸሎት ቤቱን ዘግተው ለጸሎት የሚመጡትን ሰዎች እየያዙ ይደበድቡ ነበር። እኛም ሃይሴ የሚባል ቦታ ወዳለ ጸሎት ቤት ሄደን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰንበት አምልኮ ተካፈልኩ። ሌንጂሶ የሚባል አገልጋይ የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12፣ 13-21 ያለውን የሃብታሙን ሰው ታሪክ አስተማረ።

እኔና ሊረሞ ወደ ሰፈራችን ስንመለስ በሰማነው ስብከት ላይ እየተወያየን ነበረ። እኔም "በሃብታሙ ሰው ሕይወት እንደሆነው ዛሬ የኔ ነው ያልኩት ሁሉ ለካስ ነገ የኔ አይደለም።" እያልኩ አሰብኩ።

ከዚያ በኂላም በብዙ ደስታ እና ምስጋና በተለመደው ትጋት የምሠራውን የግብርና እና የእረኝነት ሥራዬን ቀጠልኩ። በዚሁ ጊዜ ትንሽ ቆየት ብለው የእኔ መንፈሳዊ አባት የሆኑት ጋሼ ሳህሌ እና ሌሎች አገልጋዮች ከከምባታ ወደ እኛ አካባቢ እየመጡ በማገልገል እኛንም በመንፈሳዊ ሕይወት እንድናድግ ማስተማር መጀመራቸው እኔን በመንፈሳዊ ሕይወት እንዳድግ በጣም ረዳኝ። እኔ ያኔ ከከምባታ እየመጡ የኛን ምድር በወንጌል ያጥለቀለቁትን እነ ጋሼ ሳህሌን ሳስብ ለነዚያ ታማኝ አገልጋዮች በጣም ትልቅ አክብሮት አለኝ። ዛሬም ድረስ እነዚያ ታላላቅ የወንጌል አገልጋዮች በኛ ምድር እየተዘዋወሩ ወንጌል እንዲስፋፋ ሲለፉ ምስሉ ይታየኛል።

እኔም ባመንኩበት ጊዜ እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅ እና በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ትልቅ ጥማት ስለነበረኝ በአንድ ሳምንት ውስጥ ፊደል ቆጥሬ ጨረስኩ። ከዚያም በዛ ዘመን ብስራተ ወንጌል ተብሎ የታተመ የዮሐንስ ወንጌልን ብቻ የያዘ መጽሐፍ ስለነበር እየገዛሁ ማንበብ ጀመርኩ።

በዚሁ ወቅት እኔ በጣም ትጉህ ገበሬ ስለነበርኩ የእርሻ ሥራዬን ሳላቋርጥ በእረፍት ሰዓቴ የዮሐንስ ወንጌልን አነብብ ነበር። በዚህ ጊዜ ማታ ማታ ጋሼ ሳህሌ እኔን ጽሑፍ ለማስተማር ደግሜ እንድ ጽፈው የጻፉልኝ ፊደል ያለበትን ደብተር እና እርሳስ ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ይዤ ወደ እርሻ እሄድ ነበር። ከዚያም ደብተሩን በእርሻው አንድ ጠርዝ፤ ብስራተ ወንጌሉን በሌላ ጠርዝ አደርግ እና በእርሻው መሃል እየኮተኮትኩ ሄጄ ከአንዱ ጠርዝ ሄጄ አንዱ ጠርዝ ደርሼ ሳርፍ እጽፋለሁ ወይም አነባለሁ። ከዚህም ሌላ ቀን ላይ ጥሩ የወይራ እንጨት ፈልጬ አዘጋጅ እና ማታ ማታ ቤት ውስጥ ሰው ከተኛ በኋላ ወይራውን አንድጄ በነበልባሉ የዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍን አነብብ ነበር። በዚህ ዓይነት ሳነብ በ10 ወራት ውስጥ በእርሻ ቦታ በጭቃ እጄ ስይዛቸው እየተበላሹ እና በወይራው እሳት እየተለበለቡ ሦስት መጻሕፍት ጨረስኩኝ።

ከዚህ የግል ጥረቴ ባሻገርም ዘወትር ሐሙስ ማታ ከሌሎች ያመኑ ልጆች ጋር በአቶ እንጂሎ እናት ቤት እየተሰበሰብን ጋሼ ሳህሌ እየመጡ ያስተምሩን ነበር። በ10ኛው ወራችንም ለጥምቀት ተዘጋጀንና በታኅሣስ ወር የጥምቀት ሥርዓት ፈጸምን።

ልክ የጥምቀት ሥርዓታችን በተፈጸመበት ዕለትም በሻሾጎ ምድር ሊያገለግሉ የመጡ አገልጋዮችን አብሮ ሆኖ እያገዘ የሚዞር አገሩን የሚያውቅና መንገድ የሚመራ ሰው ተፈልጎ ጥያቄ ሲቀርብ እኔ ፈቃደኛ ሆኜ አብሬ ለማገልገል ተነሳሁ። ወዲያውኑም ሀምባኖ (ጴጥሮስ) ከሚባል አንድ የወንጌል አገልጋይ ጋር ለማገልገል ወጣን። የዛሬዋ ቡኖሻ ከተማ በተቆረቆረችበት አካባቢ ሰዎች ጤፍ በሚያጭዱበት እርሻ ላይ አብረን ጤፍ እያጨድን ለ15 ቀናት ያህል ስንመሰክር ቆየን።

በዚህ ጊዜ ጎበዝ አገልጋይ የሆነው ሀምባኖ በፍጹም ሌላ ነገር እንድንሰብክ አያደርግም ነበር። ሁልጊዜ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3፡16 ላይ ያለውንና "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለምን እንዲሁ ወዷልና።" የሚለውን ክፍል ብቻ እንሰብክ ነበር።

በዚህ መልኩ እያገለገልን እያለ አንድ ቀን ለአዳር በአቅራቢያ ወደ ነበረ የእህቴ ቤት አቶ ሃምባኖን ይዤ ሄድኩ። በዚህ ጊዜ እርሷ "ኬዳሞ የቤተሰቡን ሀብትና ንብረት ጥሎ የትም ይዞራል።" ሲባል ሰምታ ስለነበር እኔን "ቤት እና ንብረት ጥለህ እኔጋ ልታድር ትመጣለህ?" ብላ ዱላ አንስታ አባረረችኝ እና ማደሪያ ፍለጋ ወደ አንድ ክርስቲያን ቤት አመራን። እዚያም ተቀብለው አስገቡን እና ባገኘነው የሚቆረቁር ያልታሸ ቁርበት ላይ ተኝተን አደርን። በዚህ መልኩ ስናገለግል ቆይተንም ተመለስን።

እዚህጋ በመንፈሳዊ ህይወት ያሳደጉኝ ጋሼ ሳህሌ እንዴት በህይወት ምስክርነት በትጋት እንዳስተማሩኝ እና ጌታን በሙሉ መሰጠት ማገልገል እንድችል እንዴት ምሳሌ እንደሆኑኝ ልተርክላችሁ።